# የሉቃስ ወንጌል (44)

## ጥናት አንድ ሉቃስ 1፡1-25

የጥናት ዓላማ፡- አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሄር ፊት በጽድቅና እርሱን በመፍራት መመላለሳችን እርሱን ደስ የሚያሰኝ ነገር ቢሆንም እንኳን፤ በዚህች ምድር ለምንኖረው ኑሯችን መሳካት ግን ዋስትና ሊሆነን እንደማይችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ሁለቱም የጌታን ትዕዛዝና ሥርዓት ሁሉ ጠብቀው ያለነቀፋ የሚኖሩ፣ በእግዚአብሄር ፊት ጻድቃን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ ኤልሳቤጥ መካን በመሆኗ ልጅ አልነበራቸውም፡፡››

1. የሉቃስ ወንጌል 1፡1-25 በአንድነት ይነበብ፡፡ ሉቃስ ይህንን ታሪክ ለመጻፍ የመጀመሪያው ሰው እንዳልነበረ በምን እናውቃለን? በቁ1-2 ላይ ለኢየሱስ ሐዋርያት የሰጣቸው ሁለት ሥያሜዎች ምንና ምንድናቸው? እነዚህ ሁለት የተጠቀሱት ነገሮች ለተጻፈው ታሪክ የበለጠ ተቀባይነት ሊኖረው እንዲችል የሚያደርጉት በምን መንገድ ነው?
2. ቁ1-4ትን ስናነብ ሉቃስ በእኛ መካከል ተፈጸሙ ስለሚላቸው ነገሮች የጻፈበትን ሁኔታ ያስረዳል፡፡ የሉቃስን የአጻጻፍ ሁኔታ ያስረዳሉ የምትላቸውን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር፡፡ ጸሐፊው ይህንን ያህል ጊዜ ወስዶ በለቴዎፍሎስ መጻፍ የፈለገበትና ለነገሩ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ የፈለገበት ምክንያት ለምንድነው? አንተስ እንደ ሰዎች በያዙት እውነት ላይ እንዲመሰረቱ ምን ያህል ጥረት ታደርጋለህ?
3. ቁ5-7ትን ስንመለከት በተለይም ቁ6 ላይ ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ ምን ዓይነት ህይወት ይመሩ እንደነበረ እናያለን፡፡ ጸሐፊው ስለእነዚህ ሁለት ሰዎች በዚህ ቁጥር ላይ ምን ይናገራል? ስለ እነዚህ ሁለት ሰዎች ይህ ክፍል የሚናገራቸው ሁለት ተጨማሪ ነገሮችን ተናገር፡፡
4. ቁ8-13 ላይ ዘካሪያስ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እያለ ነበረ መልዓኩ የተገለጠለት? መልአኩ በቁ13 ላይ ‹‹…አትፍራ ጸሎትህ ተሰምቷል›› ብሎ የተናገረውን በቁ18 ላይ ዘካርያስ ከመለሰው መልስ ጋራ ስታስተያይ፤ ዘካርያስ ስለዚህ ነገር በዚያን ወቅት እየጸለየበት የነበረ ይመስልሃል ወይ? እነዚህ ባልና ሚስት ልጅ ባለመውለዳቸው በእግዚአብሄር አኩርፈው እንዳልተቀመጡ የምናውቀው እንዴት ነው? አንተ የጸለይከውን ብትረሳ፤ የተለመነውን የማይረሳ አምላክ ስላለህ በፊቱ በጽድቅ መመላለስ ቀጥል፡፡
5. ቁ14-17 ላይ ስለ ዮሐንስ የተነገሩትን ነገሮች አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር፡፡
6. ቁ18-20 ዘካርያስ በቁ18 ላይ መልዓኩን ለጠየቀው ጥያቄ መልስ አግኝቷል ወይ? ዘካርያስ በቁ18 ላይ የተናገረውን አነጋገር ከመልዓኩ አመላለስ ስንመለከት እንደምንድነው የወሰደው? ቁ20 ‹‹ጊዜውን ጠብቆ የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ›› በተለይም ‹‹ጊዜውን ጠብቆ›› የሚለው አነጋገር ስለ እግዚአብሄር የተስፋ ቃል ምን ያስተምረናል?
7. በቁ 21 ላይ የዘካርያስን ለመናገር አለመቻል ለምን ይመስልሃል ህዝቡ እግዚአብሄር እንደቀሰፈው ከማሰብ ይልቅ ራዕይ እንዳየ አድርገው የገመቱት?
8. ቁ23-25 ስናነብ ከኤልሳቤጥ አነጋገር ያለልጅ ያሳለፈቻቸው ረጅም አመታት ስላሳለፈችው ነገር ምን ይነግረናል?
9. ቁ6-7ትን መለስ ብለን ስናይ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ከእግዚአብሄር ጋራ ያላቸውን ህይወት ተመልክተን፣ በሃጥያት የሚኖሩ ሁሉ ልጅ እየተሰጣቸው እነርሱ ግን ያለልጅ የመሆናቸውን ሁኔታ ስንመለከት በአዕምሯችን ሊመጣ የሚችለው ጥያቄ ምንድነው? በጽድቅ የሚኖረው ሰው ምድራዊው ኑሮው ሳይሳካለት፣ በሃጥያት የሚኖረው ሰው ደግሞ ኑሮ አምሮለት መኖሩ ጥያቄ ፈጥሮብህ ያውቃል ወይ? በጽድቅና እግዚአብሄርን በመፍራት መኖራችን ለምድራዊ ኑሯችን መሳካት ዋስትና ሊሆንህ እንደማይችል ልትረዳ ያስፈልጋል፡፡

# ጥናት ሁለት ሉቃስ 1፡26-56

የጥናት ዓላማ፡- በእግዚአብሄር አይን ስንታይ እኛ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመንን ሁሉ በእርሱ እጅግ የተወደድን፣ ጌታ ከእኛ ጋራ መሆኑንና፣ በክርስቶስ የተባረክን ሰዎች መሆናችንን በመረዳት ስለራሳችን ያለንን አመለካከት ልንቀይር እንደሚገባን ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እጅግ የተወደድሽ ሆይ፣ ሰላም ለአንቺ ይሁን፣ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፣ አንቺ የተባረክሽ ነሽ አላት›› ሉቃስ 1፡28 ፣ 1ኛ ዮሐ 3፡1 ፣ ማቴ 28፡20፣ ኤፌ 1፡3

1. ሉቃስ 1፡26-56 በአንድነት ይነበብ፡፡ ዮሐንስና ኢየሱስ ክርስቶስ ዕድሜአቸውን አስመልክቶ በስንት ዓመታት ነው የሚበላለጡት? በቁ26 ላይ ስለ መልአኩ ገብርኤል የምናነበው ሃሳብ በዕብ 1፡14 ላይ ጸሐፊው የተናገረውን ሃሳብ እውነተኛነት ማረጋገጫ የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ቁ28-29 ላይ መልአኩ ገብርኤል ስለ ማርያም የሚናገራቸው ቢያንስ ሶስት ነገሮችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር፡፡ ከነዚህ ስለ ማርያም ከተነገሩት ነገሮች መሃል ማርያም ከሰራችው ወይም ካደረገችው ነገር ጋራ የሚገናኝ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት ቻልክ? ማርያም በመልአኩ አነጋገር እጅግ በጣም እንደደነገጠች ቁ29 ይነግረናል፡፡ ለምን ይመስልሃል ማርያም የመልአኩ አነጋገር ያስደነገጣት?
3. በቁ30-33 ከምናነበው ማርያም እንዳትፈራ ምክንያት አድርጎ መልአኩ ገብርኤል የነገራት አንድ ነገር ምንድነው? በማርያም ህይወት በቅርቡ የሚከናወኑና መልአኩ አስቀድሞ ያበሰራት ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር፡፡ ከማርያም ስለሚወለደው ልጅ ማንነትና ምንነቱን አስመልክቶ የተዘረዘሩት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
4. ዘካርያስ በቁ18 ላይ ጥያቄው እንደ አለማመን እንደተቆጠረበት ተመልክተናል፤ በቁ34-38 ላይ መልአኩ የማርያምን ጥያቄስ እንደ አለማመን ቆጥሮታል ወይ? ይህንን ለማለት ያስቻለህን ምክንያት ተናገር፡፡ በቁ38 ላይ ማርያም ከተናገረችው አነጋገር ምን መረዳት እንችላለን? አንተስ እግዚአብሄር በቃሉ ለተናገረህ የተስፋ ቃል ምላሽህ እንደ ዘካርያስ ይሆን ወይስ እንደ ማርያም?
5. በአንተ አመለካከት የማርያምና የኤልሳቤጥን ልጆች ሁለቱንም የተአምራት ልጆች የሚያሰኛቸው ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
6. በቁ29 ላይ የመልዓኩ የገብርኤል ሰላምታ በማርያም ህይወት ውስጥ የፈጠረው ስሜትና፤ በቁ40-41 ላይ የማርያም ሰላምታ በኤልሳቤጥ ቤት ውስጥ የፈጠረው ስሜት ምን ሆኖ ነው የምታየው? እዚህ ሥፍራ ላይ የማርያም ወደ ኤልሳቤጥ መግባት ወደ ቤቱ ደስታን ሊያመጣ የቻለበት ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ? የኢየሱስ ወደ ውስጥህ መግባት በአንተስ ህይወት ውስጥ የሚያዘልል ደስታን አስከትሏል ወይ?
7. ቁ42-45 ያሉትን ቁጥሮች ስንመለከት ኤልሳቤጥ ጌታ በማለት የተቀበለችው ማንን ነው? ኤልሳቤጥ ስለማርያም ስላላት አመለካከት እነዚህ ክፍሎች የሚነግሩንን ሃሳቦች አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር፡፡ አንተስ ስለማርያም ያለህ አመለካከት ከኤልሳቤጥ አመለካከት ጋራ ስታገናዝበው ምን ይመስላል?
8. መለስ ብለን ቁ28ትን ስንመለከት ስለማርያም መልአኩ የተናገራቸው ሶስት ሃሳቦች በክርስቶስ ላመኑት ሁሉ የሚሆን ትክክለኛ መግለጫ መሆኑን ማረጋገጥ እንዴት እንችላለን? ለማርያም የተባሉት ሶስቱም ነገሮች በክርስቶስ በኩል ላንተም እውነት እንደሆኑ ትረዳለህ ወይ? በክርስቶስ በኩል ሆነን እኛ በእርሱ ያመንን ሁላችን በእግዚአብሄር እጅግ የተወደድን፣ ጌታ ከእኛ ጋራ ያለና፣ የተባረክን ሰዎች መሆናችንን ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡

# ጥናት ሶስት ሉቃስ 1፡46-80

የጥናት ዓላማ፡- ማርያም በዙሪያዋ የምትሰማውን ድምጽ ሁሉ አሸንፋ ከእግዚአብሄር እንደሆን የተረዳችው እውነት ለመቆም እንደቆረጠች፤ እኛም ከአካባቢያችን የሚመጣውን ድምጽ ሁሉ መስማት ትተን የእርሱን ሃሳብ ለመከተል መወሰን እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…በአባቱ ስም ዘካርያስ ሊሉት ፈለጉ፤ እናቱ ግን አይሆንም፣ ዮሓንስ መባል አለበት አለች። እነርሱም ከዘመዶችሽ በዚህ ስም የተጠራ ማንም የለም አሏት።" ሉቃ 1፡59-61

1. ሉቃስ 1፡46-80 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ46-55 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ማርያም ስለእግዚአብሄር ስትዘምር የጠቀሰቻቸው ቢያንስ ሶስቱን የእግዚአብሄር ባህርያት ተናገር፡፡ በቁ54-55 መሰረት እግዚአብሄር ይህንን መልካም ነገር ለማድረግ የተነሳሳበት ዋነኛ ምክንያት ምንድንው? እግዚአብሄር በገባው ቃልና፣ ነገሩ በተፈጸመበት መሃል ያለውን ርቀት በግምት ለመናገር ሞክር።
2. ቁ57-58ትን ስንመለከት የኤልሳቤጥ ጎረቤቶችና ዘመዶችዋ በእርስዋ ህይወት የሆነውን ነገር የተመለከቱት በምን መንገድ ነበረ? ለኤልሳቤጥ በሆነላት ነገር እነዚህ ጎረቤቶቸና ዘመዶች ያሳዩት ስሜት ምን ይመስላል? አንተስ እግዚአብሄር ለወንድሞችህ ወይም ለእህትህ በሚያደርገው ነገር አብረህ ደስ ትሰኛለህ ወይስ ቅናት ያቃጥልሃል?
3. ዘካርያሰ የልጁ ስም ማን እንዲባል ነው የፈለገው? ባልና ሚስት የልጁን ስም በተመለከተ ወደ አንድ አይነት ስም የመጡበት ምክንያት ለምንድነው? አባትየው ስም ሲያወጣ በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች ያስደነቀው ነገር ምን ይመስልሃል?
4. ዘካርያስ የልጁን ስም "ዮሐንስ" ብሎ በመጻፉና ወዲያው አፉ በመከፈቱ መሃል ያለው ግንኙነት ምን ይመስልሃል? ካህኑ ዘካርያስ የአፉን መከፈት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያገኝ የተናገረው ምን አይነት ነግግር ነበረ? ይህ ሰው አለማመን አፉ መዘጋትና በመታዘዙ ምክንያት ደግሞ አፉ መከፈቱ ምን መማር እንችላለን?
5. በማርያም ዝማሬ በተለይም ቁ54-55 እና በዘካርያስ ትንቢት በተለይም ቁ72-73 በመመልከት በሁለቱ መሃል የምታያቸውን መመሳሰሎች በመዘርዘር ተናገር።
6. ዘካርያስ በቁ74 እና 74 ላይ የተናገረው ትንቢት በተወለደው ልጅ በዮሓንስ ህይወት ውስጥ በምን መንገድ ሊፈጸም እንደሚችል አስረዳ። ያለፍርሃት እንድታገለግለው ከጠላትህ እጅ ነጻ ያወጣህን እግዚአብሄር እያገለገልከው ትገኛለህ ወይ?
7. ቁ78-80 ያለውን ክፍል ስናነብ ዘካርያስ ከተወለደው ልጅ ማንነትና ሊሰራ ካለው ነገሮች በስተጀርባ የሚመለከተው ማንን ይመስልሃል? ምናልባትም በዘመኑ የነበሩት ሰዎች ያላስተዋሉት፣ ይህ ሰው ግን የተረዳውና በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚናገራቸው ምን ነገሮች ታያለህ?
8. በቁ59-61 ተመልሰን ስናነብ ከላይ በልጁ መወለድ የደስታዋ ተካፋይ የነበሩት እነዚያው ሰዎች ሊያደርጉ ሲሞክሩ የምናያቸው ምን ሲያደርጉ ነው? ማርያም በዚህን ጊዜ ማድረግ የምትችላቸውና የነበራት ሁለት አማራጮች ምንና ምን ነበሩ? ማርያም የትኛውን አማራጭ ስትመርጥ ነው የምናያት? አንተስ እግዚአብሄር እንድታደርገው ካዘዘህ ነገር ይልቅ የጓደኛ ወይም የአካባቢህን ሃሳብ የምታስተናግድበት ጊዜ አለ ወይ? ከወዳጅ፣ ከጓደኛ፣ ወይም ከዘመድ የምታገኘው ምክርና ሃሳብ የእግዚአብሄርን ቀጥተኛ ትእዛዝ እንዳትከተል እንቅፋት እንዳይሆኑብህ ልትጠነቀቅ ይገባሃል።

# ጥናት አራት ሉቃስ 2፡1-24

የጥናት ዓላማ፡- ህይወታችን በተራራ ላይ ሆኖ እንዲቆይ የሁላችንም ፍላጎት ቢሆንም እንኳን፤ እንደ እነ ጴጥሮስ ለእኛ በዚህ መሆን ይሻለናል ከምንልበት ተራራ ወርደን ዝቅ ባለው ስፍራ ደግሞ መኖርንም መለማመድ ከክርስትና ህይወት አንዱ ክፍል እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እረኞቹም ሁሉም ነገር እንደ ተነገራቸው ሆኖ በማግኘታቸው፣ ስለሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሄርን እያከበሩና እያመሰገኑ ተመለሱ።" ሉቃ 2፡20

1. ሉቃስ 2፡1-24 በአንድነት ይነበብ፡፡ አሁን ባነበብነው ምንባብ ውስጥ የምናያቸው ተዋናኞች እነማን እንደሆኑ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር። ቁ1-7ን ሰናነብ፣ ለዮሴፍና ለማርያም ወደ ቤተልሄም ጉዞ ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበረ?
2. በቁ2 ላይ እንደምናነበው የዚህ ዓይነት ቆጠራ የተካሄደው ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደነበረ እንመለከታለን። በታወጀው ዓዋጅ  ዙሪያ ያሉትን ሁኔታዎች ሁሉ ስንመለከት፤ በተለይ በዚያን ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ የቄሳር ትእዛዝ መውጣት የእግዚአብሄርን ሃሳብ ማስፈጸሚያ የወጣ ዐዋጅ አድርጎ ማየት የሚያስችለን ምክንያት ምን ይመስልሃል?
3. እግዚአብሄር ይህንን የንጉሱን አዋጅ ሰማያዊ አጀንዳውን ለማስፈጸም ተጠቅሞበታል ካልን፤ በቁ1-7 ውስጥ በተካሄደው ታሪክ ውስጥ ተፈጻሚነትን አግኝቷል የምትለውን ትንቢት ተናገር። ሉቃ 1፡8-12 ትንና ሉቃ 2፡8-10 ስናነብ መልአክ ለዘካርያስና ለእረኞች ሲገለጥ እንመለከታለን። በነዚህ ክፍሎች መሃል የምታያቸውን ተመሳሳይነትም ሆነ ልዩነቶች ተናገር። እረኞቹ የእለት ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ሳሉ ጌታ እንደተገለጠላቸውና እንደተናገራቸው ማየታችን ምን ሊያስተምረን ይገባል ትላለህ?
4. በቁ8-11 ላይ መልአኩ ወደ እረኞቹ መጥቶ ያደረጋቸውና ሲሆኑ የምታያቸውን ነገሮች ዘርዝር። መልአኩ ስለተልእኮው ሲናገር ምን በማለት ነው ለእረኞቹ የገለጠው? የዚህ ህጻን መወለድ ለህዝብ ሁሉ የሚሆን ደስታን ሊያመጣ የሚችልበትና የምስራች ሆኖ ሊነገር የቻለበት ከክፍሉ ስታነብ ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? በዚህ ህጻን መወለድ ምክንያት በአንተስ ይህታላቅ ደስታ ተገልጦ ይታያል ወይ?
5. ቁ13-15ትን ስናነብ እነዚህ እረኞች ሌላ ያጋጠማቸው ነገር ምን ታያለህ? እረኞቹ የእነዚህን የመላእክት መገለጥና አስቀድሞ የምስራች የተናገራቸውን መገለጥ ሁሉ ምንጩን ከየት እንደሆነ ነው የተገነዘቡት? እረኞቹ በመላእክቱ የተነገራቸውን ለሰዎች ሁሉ የሚሆነውን የምስራች አምነው እንደተቀበሉ በምን ማወቅ ይቻላል?
6. ቁ16-19 ላይ እረኞቹ ያደረጓቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እረኞቹ እግዚአብሄር ያሳያቸውን መገለጥ ሲናገሩ የሰዎቹ ሁኔታውን አቀባበል ምን ይመስል እንደነበረ አስረዳ።
7. በሉቃ 1፡59-63 ላይ ስለምጥምቁ ዮሓንስ ስም አወጣጥና በዚህ ክፍል ማለትም በሉቃ 2፡21 ላይ በሰፈረው ህጻን ስም አወጣጥ ላይ የምታያቸውን ማንኛቸውንም ተመሳሳይነቶችም ሆኑ ልዩነቶች በማነጻጸር ተናገር። ሉቃ 2፡22-24 ከምናነበው፤ ማርያምና ዮሴፍ ያኔ ማደርያ አጥተው የተቸገሩበትና በከብት ማደሪያ ውስጥ ወዳደሩበት ከተማ ለምንድነው ለምንድነው ደግመው ለመሄድ የወሰኑት?
8. ቁ20ን መለስ ብለን ስንመለከት እረኞቹ እግዚአብሄር ከተናገራቸው ነገሮች ምን ያህሉ ናቸው እውነት ሆነውና ተፈጽመው ያገኙት? አስደናቂ የሆነው ሰማያዊ መገለጥ ሁሉ ካለቀ በኋላ እረኞቹ ተመልሰው እንደሄዱ የሚነግረን ወደየት ነው? በነበሩበት ሁኔታ ውስጥ ቢቆዩ የሚወዱ ይመስልሃል ወይ? ለምን? አንዳንዴ  እንደእነ ጴጥሮስ ለእኛ በዚህ መሆን ይሻለናል ሊያሰኙ የሚያስችሉ ወቅቶች ቢኖሩም፤ ለበጎቹ የእረኞቹ መመለስ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ፤ አንተም ነገሮችን ከዚህ እውነት አንጻር ልትመለከት ያስፈልግሃል።

# ጥናት አምስት ሉቃስ 2፡25-52

የጥናት ዓላማ፡- የሰዎችን ልብ የሚያውቀው ኢየሱስ እንኳን መልስ ከመስጠቱና ለማስረዳት ከመሞከሩ በፊት ያስቀደመው እነርሱ የሚናገሩትን ማዳመጥ ከሆነ፤ እኛም ለሰዎች መልስ ለመስጠት ሳንቸኩል ሃሳባቸውን ማዳመጥ እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ከሶስት ቀንም በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸውና ጥያቄ ሲያቀርብላቸው በቤተ መቅደስ ውስጥ አገኙት፤ የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ይደነቁ ነበር።” ሉቃ 2፡46-47 ፣ ምሳ 18፡13

1. ሉቃ 2፡25-52 በአንድነት ይነበብ። በቁ25 ላይ ብቻ በመመስረት ይህ ስምዖን የተባለው ሰው ምን አይነት ሰው እንደነበረ በዝርዝር ተናገር። ቁ25ት ላይ ስለ ስምዖን ሲናገር “መንፈስ ቅዱስ በላዩ ያደረ ሰው ነበረ” ይላል፤ መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ የአዲስ ኪዳን ክርስትያን ከስምዖን የሚለይበት መንገድ ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነህ የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ ሆነሃል ወይ?
2. “መንፈስ ቅዱስ” የሚለው አነጋገር ከስምዖን ጋራ በተገናኘ መንገድ በቁ25-27 ውስጥ ብቻ ስንት ጊዜ ተጽፎ እናገኘዋለን? በእስራኤል ብዙ ሰዎች ሲኖሩ መንፈስ ቅዱስ ለምን ይመስልሃል ስምዖንን ብቻ መርቶ ኢየሱስ ወደነበረበት ቤተ መቅደስ መርቶ ያመጣው? ስምዖንን ኢየሱስን ከወላጆቹ ተቀብሎ ሲያቅፈው ምን ዓይነት ስሜት ሊሰማው እንደሚችል ተናገር።
3. በቁ29 ላይ “ጌታ ሆይ ቃል በገባኸው መሰረት” በማለት ስምዖን የሚናገረውን እናነባለን፤ ጌታ ለዚህ ሰው የገባው ቃል ምን የሚል ነበረ? ቁ29-32 ላይ ስምዖን ኢየሱስን አህዛብንና እስራኤልን አስመልክቶ ምን በማለት ነው የሚገልጠው? ይህንን ህጻን ካየና ካቀፈው በኋላ ስምዖን ለእግዚአብሄር የሚነግረው ምን እንዲያደርግ ነው? ለአንተስ ኢየሱስን ማየትህና ማግኘትህ በቂ ነገር ሆኖልህ ከእንግዲህ ጌታ ቢወስደኝም ይበቃኛል ወደሚለው አስተሳሰብ ደርሰሃል ወይ?
4. በቁ33-35 ውስጥ በዚህ ህጻን ምክንያት ሊመጡ እንዳሉ የተነገሩት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር። “የብዙዎችም የልብ ሃሳብ የተገለጠ እንዲሆን” በማለት የተነገረው ትንቢት ምን ማለት እንደሆነ ነው የምትረዳው?
5. በቁ36-38 ላይ ስለምናየት ሴት ማንነት፣ ምንነትና ማናቸውንም ስለእርሷ ከክፍሉ የምታያቸውን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። ቁ38 ላይ “የኢየሩሳሌምን መቤዥት ለሚጠባበቁ ሁሉ ሰለ ህጻኑ ተናገረች።” ይላል። የኢየሩሳሌምን መቤዥት ከሚጠባበቁ ሰዎች መሃል አንድ ሰው ጥቀስ ብትባል ማንን ትጠራለህ? ቁ37 ጾምና ጸሎትን እንደምን አድርጎ ነው የሚያቀርብልን? አንተስ ለእግዚአብሄርን ቤትና ለህዝቡ ራስህን በጾምና በጸሎት የምትጋደለው ነገር አገልግሎት እንደሆነ ተረድተሃል ወይ?
6. በቁ39-40 ላይ ስናነብ፤ የኢየሱስ እናትና አባት ከእግዚአብሄር ጋራ ስለነበራቸው ግንኙነት ምን ይጠቁመናል? በህጻኑ ሰውነትና ማንነት ላይ እየሆነ ያለው ነገር ምን ነበረ? በዮሴፍና በማር ያም የምናነበው የእግዚአብሄርን ህግ ሙሉ ለሙሉ የመታዘዝ ትጋት በአንተ ህይወትስ ምን ያህል ትጋት ታሳያለህ?
7. ቁ41-52 በአንድነት በማንበብ በተለይ ቁ48 ላይ እናቱ ማርያም ለጠየቀችው ጥያቄ የኢየሱስ መልስ ምን ነበረ? የመለሰላቸው መልስ እንዳልገባቸው ክፍሉ ያረጋግጥልናል፤ አባትና እናቱ ከኢየሱስ አነጋገርና መልስ ያልተረዱት ሃሳብ ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
8. ቁ41-47ትን ስናነብ ከወላጆቹ ጠፍቶ የነበረው ኢየሱስ የተገኘው የትና ምን እያደረገ ነው? በተለይ ቁ46-47ትን በጥንቃቄ ስንመለከት ኢየሱስ ከእነዚህ ሰዎች ጋራ ያደርግ የነበራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
9. ኢየሱስ ከመምህራኑ ጋራ ባካሄደው ውይይት የሶስቱን ነገሮች ቅደም ተከተል በማስተዋል ስንመለከት ቅድሚያ ተሰጥቶት የምናየው ነገር ምንድነው? አንተስ ከሰዎች ጋራ በምታካሂደው ውይይት ቅድሚያ ስትሰጥ ራስህን የምታገኘው ከሶስቱ ለየትኛው ነው? ከሰዎች ጋራ ለምታደርገው ማናቸውም ውይይት አስቀድመህ ነገሩን ሳትረዳ መልስ ለመስጠት ከመቸኮልህ በፊት ሃሳባቸውን ለመረዳት ጊዜ በመስጠት ማዳመጥ መልካም ነው። (ምሳ 18 ፡13)

# ጥናት ስድስት ሉቃስ 3፡1-37

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ቃል፤ ሰዎች ለባለ ስልጣናትና ለነገስታት ይገዙ ሲል፤ የሚያደርጉትን ክፋትና ሃጥያት አይተው እንዳላዩ ሆነው እንዲያልፉ ማለቱ ሳይሆን፣ የእግዚአብሄር ሰው እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ስለሃጥያታቸው ፊት ለፊት በመገሰጽ በጽድቅ እንዲኖሩና በጽድቅ እንዲፈርዱ የመናገር ሃላፊነት እንደሚጠበቅበት ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ነገር ግን ዮሐንስ የአራተኛውን ክፍል ገዥ ሄሮድስን የወንድሙ ሚስት በነበረችው በሄሮድያዳ ምክንያትና ስለሌሎች ስራዎቹ በገሰጸው ጊዜ … ዮሐንስን ወህኒ ቤት አስገባው።" ሉቃ 3፡19-20

1. ሉቃስ 3፡1-37 በአንድነት ይነበብ። መጥምቁ ዮሓንስ አገልገሎቱን የጀመረበት ጊዜ ለማወቅ አስቸጋሪ የማይሆንበት ምክንያት ለምንድነው? ቁ1-3ትን ስናነብ ዮሐንስ ከምድረበዳ ወደ መንደሮቹ መጥቶ አገልግሎቱን ገና ሲጀምር ይዞ የተነሳው መልእክት ምን የሚል ነበረ?
2. በቁ7-9 ላይ ንስሃ ለመግባትና ለመጠመቅ ወደ ዮሐንስ የመጡት ሰዎች ከንስሃው በተጨማሪ የተጠየቁት ነገር ምን ታያለህ? ዮሐንስ "እንግዲህ ለንስሃ የሚገባ ፍሬ አፍሩ" ብሎ ሲነግራቸው ምን ማለቱ ይመስልሃል? "ደግሞም በልባችሁ አብርሃም አባታችን አለን ማለትን አትጀምሩ" የሚለው አነጋገር እንዴት ትረዳዋለህ? የአንተን ንስሃ ስትመለከተው የንስሃ ፍሬ ያለው ሆኖ ታየዋለህ ወይ?
3. ቁ10-11ድን ስናነብ ህዝቡ የንስሃ ፍሬ ለማፍራት ልቡ የተዘጋጀ እንደሆነ መናገር የሚያስችለን ነገር ምንድነው? ለህዝቡ ጥያቄ ዮሐንስ የሰጠው መልስ ምን የሚል ነው? ይህንን ክፍል ስንመለከት የዮሓንስ ትኩረት ሰዎች ከሁለት በላይ የሆነ ነገር እንዳይኖራቸው ማለቱ ነው ወይ? ካልሆነስ ሊያስተምር የፈለገው እውነት ምንድነው ትላለህ?
4. ቁ10-14ትን ስንመለከት የንስሃ ጥምቀት ለመጠመቅ የመጡት የሰዎች አይነት ምን ምን አይነት እንደነበረ ዘርዝር። ቀረጥ ሰብሳቢዎቹ ወደ ዮሐንስ ከመምጣታቸው በፊት በተሰለፉበት የስራ መስክ ያደርጉ የነበረው ሃጥያት ምን ነበረ? ቀረጥ ሰብሳቢዎችንና ወታደሮችን ከህዝብ መሃል ለይቶ ለብቻቸው ማሳየት የፈለገበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?
5. ንስሃ ለመግባትና ለመጠመቅ የመጣ ወታደር የንስሃ ፍሬ አፍርቷል ማለት የሚቻለውና በሰው ፊት ግልጽ ሆኖ የሚታየው ነገር ምን ሲያደርግ ነው ብለህ ታምናለህ?
6. ይህ ሁሉ የንስሃ ጥምቀትና ጥያቄና መልስ ሁሉ ሲካሄድ ሳለ በህዝቡ ሃሳብ ውስጥ ይመላለስ የነበረው ጥያቄ ምን ነበረ? ይህ በህዝቡ አእምሮ ውስጥ እየተመላለስ ያለው ሃሳብ ለዮሐንስ አደገኛና ለውድቀቱ ሊሆን የሚችለው በምን መንገድ ነው?
7. በቁ16-18 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ከእርሱ እንደሚበልጥ የተናገረባቸውን ቢያንስ አራት መንገዶች ተናገር። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለይም በቁ18 ላይ ዮሐንስ ያደርግ የነበረውን ድርጊት ምን በማለት ነው ያስቀመጠው?
8. በዚህ በሉቃ 3፡19 ላይ መጥምቁ ዮሓንስ ያደረገው ድርጊት በሮሜ 13፡1 ላይ "ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ስልጣኖች ይገዛ" ተብሎ ከተጻፈው ሃሳብ ጋራ ስትመለከተው ዮሐንስ የእግዚአብሄር ህግ ተላልፏል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? ነገስታትን ማክበርና መታዘዝ ማለት ሃጥያታቸውን፣ ፍርደ ገምድልነታቸውን አይተው እንዳላዩ ሆኖ የማለፍ ነገር እንዳልሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።

# ጥናት ሰባት ሉቃስ 4፡1-19

የጥናት ዓላማ፡- የጌታን መንፈስ መቀበላችንና መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖሩ ለመኩራሪያና ለጉራ ሳይሆን፤ አማኝ በሙሉ በክርስቶስ ወንጌል ብቻ ሊገኝ የሚችለውን ነጻነት በሰይጣን እስራት ውስጥ ላሉትና ጠላት አይኖቻቸውን ላሳወራቸው ሁሉ የምስራቹን ለማወጅ እንዲችል ለማብቃት መሆኑን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድሆች ወንጌልን እንድሰብክ እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም ማየትን እንዳውጅ፣ የተጨነቁትን ነጻ እንዳወጣ፣ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል።" ሉቃ 4፡18-19

1. ሉቃስ 4፡1-19 በአንድነት ይነበብ። በሉቃ 3፡22 ላይ ስለ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ምስክርነት ምን የሚል ነበረ? በሉቃ 4፡1-2 ላይ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ወደ ምድረበዳ የወሰደበት ምክንያት ለምን ነበረ? እግዚአብሄር የሚወደውና በእርሱ ደስ የሚለው ሆኖ እያለ በሰይጣን እንዲፈተን መፍቀዱ ለአንተና ለእኔ ምን ሊያስተምረን እንደሚችል ተናገር።
2. የመጀመሪያው ኢየሱስ የቀረበለት ፈተና ምን የሚል ነበረ? የእግዚአብሄር ልጅነቱን እንዲያረጋግጥ የተጠየቀው ምንን በመፈጸም ነበረ? በሉቃ 3፡22 ላይ እግዚአብሄር ስለዚህ ጉዳይ አርጋግጦ የተናገረው ምን በማለት ነበረ? አንተስ እግዚአብሄር በቃሉ በግልጽ ልጄ ነህ ብሎ የነገረህን እውነት እንድትጠራጠር ያደረገህ ጊዜ አለ ወይ? የእግዚአብሄር ልጅነትህን የሚያረጋግጥልህ የእግዚአብሄር ቃል እንጂ አንተ ማድረግ የምትችለው ወይም የማትችለው ነገር አይደለም። 1ኛ ዮሐ 3፡1 ተመለከት።
3. በቁ6-8 ላይ ዲያቢሎስ "የእነዚህ መንግስታት ስልጣንና ክብር ሁሉ ለእኔ ተሰጥቷል" በማለት የተናገረው አነጋገር ትክክልና እውነተኛ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን? በዚህ ክፍል ኢየሱስ ስግደት ሊሰጠው የሚገባው ለማን እንደሆነ ነው የሚናገረው? ራዕ 22፡8-9 ላይ የምናነበው ጥቅስ በምን መንገድ ነው ይህንን ሃሳብ የሚደግፈው?
4. ቁ9-12 ላይ ዲያቢሎስ ሶስተኛ ፈተናውን ሲያቀርብ እንመለከታለን። ይህ ሶስተኛው ፈተና ከቀደሙት ሁለት ፈተናዎች የሚለይበት አንድ ዋና ነገር አልው፤ ይህ ፈተና ከሌሎቹ የሚለየው በምን መንገድ ነው? ይህ ዓይነቱ ፈተና ለአንተ ወይም ለእኔ ቢቀርብልን ከባድ ሆኖ የምናገኘው ለምን ይመስልሃል?
5. ቁ9-13 ላይ ስንመለከት ዲያቢሎስ ኢየሱስን መፈተን ያቆመው መቼ ነው? ይህንን ማለቱ ኢየሱስ ከአሁን በኋላ ፈተና የሚባል ነገር አይገጥመውም ማለት ነው ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ ተናገር። እኛም በህይወታችን ዛሬ በፈተና ውስጥ ባንሆንም እንኳን ጠላታችን ዲያቢሎስ አመቺ ጊዜ እየጠበቀ እንጂ ጨርሶ እንደማይተወን ልንገነዘብ ያስፈልገናል።
6. ኢየሱስ በዲያቢሎስ መፈተኑን ከጨረሰ በኋላ በቁ14-15 ውስጥ የሆነውንና ያደረጋቸውን ነገሮች ዘርዝር። ቁ15ትን ስናነብ ከሚናገራቸው ነገሮች መሃል "በምኩራባቸው ያስተምር ነበር" ይላል፤ ከላይ ባሉት ቁጥሮች በፈተናው ጊዜ የሰጣቸው መልሶች ኢየሱስን ለአስተማሪነት ብቁ የሚያደርጉት በምን መንገድ ነው?
7. ኢየሱስ በምድር በሚመላለስበት ወቅት በመውጣቱና በመግባቱ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን ይለማመድ እንደነበረና ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ቅርብ በሆነ ግንኙነት ይመላለስ እንደነበረ ዛሬ ካነበብነው ክፍል የሚያረጋግጡልን ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?
8. የጌታ መንፈስ በኢየሱስ ላይ በመኖሩ በምድር እንዲያከናውን ስለተቀበለው ተልዕኮ በቁ18-19 ያሉት ክፍሎች ምን ይነግሩናል? ጌታ መንፈስ በእኔ ላይ አለ ካልክ እነዚህ ተልዕኮዎች የአንተም ተልዕኮዎች እንደሆኑ ገብቶሃል ወይ? የጌታን መንፈስ የተቀበለና መንፈስ ቅዱስ በውስጡ የሚኖር አማኝ ሁሉ በወንጌል የሚገኘውን ነጻነት ለህዝብ ሁሉ የማወጅ ሃላፊነት እንዳለበት ሊገነዘብ ያስፈልጋል።

# ጥናት ስምንት ሉቃስ 4፡20፡44

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ ለናዝሬት ከተማ ህዝብ መስማት የሚፈልጉትን በደስታ ተቀብለው የማይመቻቸው እውነት ሲመጣ ትክክለኛው ማንነታቸው እንደተገለጠ ሁሉ፤ እኛም ለሰዎች መስማት የሚወዱትን ነገር ብቻ ሳይሆን የሚቆረቁርና የማይመቻቸውንም እውነት ጭምር መናገር እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ሁሉም ስለ እርሱ በበጎ ይናገሩ ነበር…በምኩራብ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ በቁጣ ገነፈሉ፤ ከተቀመጡበትም ተነስተው ከከተማው አስወጡት” ሉቃ 4፡22፣ 28-29

1. ሉቃስ 4፡20-44 በአንድነት ይነበብ። ቁ20-22ትን ስናይ፤ በናዝሬት ከተማ ነዋሪዎች መሃል ስለ ኢየሱስ ከህዝቡ ይሰማ የነበረው ነገር ምን ነበረ? ይህ ሁሉ መልካም ነገር በእርሱ ውስጥ እየተመለከቱ ለህዝቡ ኢየሱስን በሙሉ ልባቸው እንዳይቀበሉት ትግል የሆነባቸው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስ በቁ21 ላይ “ይህ የሰማችሁት የመጽሃፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ” በማለት ለህዝቡ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
2. ቁ23-24 በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ በህዝቡ ልብ ውስጥ የነበረውን ሃሳብ ምን በማለት ነው የነገራቸው? ነብይ በገዛ አገሩ እንደማይከበር ለማስረዳት የተጠቀመባቸው የሁለቱ ነብያት ስም ማንና ማን ይባላል?
3. ቁ25-27 ላይ ነብዩ ኤልያስና ነብዩ ኤልሳዕ ያደረጉትን ነገር በአጭሩ በራስህ ቋንቋ ተናገር። ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህ ሁለት ነብያት ያደረጉትን ድርጊት ተጠቅሞ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምን ነበረ? ይህ የኢየሱስ መል ዕክት በሰሚዎቹ ዘንድ ምን ያህል ተደማጭነት ያስገኘለት ይመስልሃል?
4. ቁ31-32 ላይ ኢየሱስ ከናዝሬት ከተማ ወጥቶ የገባባት ከተማ ስም ማን ይባላል? የዚህች ከተማ ስም በዛሬው ምንባባችን ውስጥ የተጠራበት ስፍራ ትናገር። ኢየሱስ በዚያች ከተማ ውስጥ ህዝቡን ያስተምር እንደነበረ እናያለን፤ ከኢየሱስ ትምህርት ህዝቡን ያስደነቀው ነገር ምኑ ነበረ?
5. ቁ33-37 የሰፈረውን ታሪክ ስናይ፤ ጋኔን ያደረበት ሰው ኢየሱስ መጥቶ ነጻ እስኪያወጣው ድረስ ይገኝ ስለነበረበት ስፍራ ክፍሉ ምን ይነግረናል? ጋኔኑ በእውቀት ደረጃም ቢሆን ስለኢየሱስ የሚያውቀውና በህዝቡ ፊት የተናዘዘው እውነት አለ፤ ይህ እውነት ምን እንደሆነ ተናገር። በስፍራው የነበሩት ሰዎች እንደተገረሙ እናነባለን፤ በስፍራው ከሆነው ነገር ሁሉ እነዚህን ሰዎች ያስገረማቸው ምኑ ነበረ?
6. በቁ38-41 ባሉት ቁጥሮች ላይ ስንመለከት ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሳቸው ከምን ዐይነት ነገሮች ነው? ፈውሱን ለመስጠት የተጠቀመባቸው ቢያንስ ሁለት መንገዶች እናያለን፤ እነዚህ ሁለት መንገዶች ምን እንደሆኑ ተናገር። በዚህ ክፍል ውስጥ የተፈወሰችው የስምዖን አማት ምስጋናዋን የገለጸችው በምን መንገድ ነበረ? አንተስ እግዚአብሄር በህይወትህ ለሰራው መልካም ስራ ምስጋናህን እርሱን በማገልገል እንደምትወደው ገልጸህለታል ወይ?
7. ኢየሱስ ከህዝቡ ተለይቶ ወደ ገለልተኛ ቦታ ዘወር እንዳለ እናነባለን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ባይጻፍም እንኳን ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታችን ስናስታውስ፤ ለምን ይመስልሃል ኢየሱስ ወደ ገለልተኛ ቦታ ዘወር ማለት ያስፈለገው? ኢየሱስ በዚህ ክፍል የተላከበት አላማ ምን እንደሆነ ነው ለህዝቡ የተናገረው?
8. መለስ ብለን ቁ22ትን ስናይ፤ ስለኢየሱስ መልካም ሲናገሩ የነበሩት ሰዎች በቁ28-29 ላይ ተገልብጠው ኢየሱስን ሊገድሉት ሲሞክሩ ይታያል። ከማሞገስ ወደ ጥላቻ በዚህ ፍጥነት ሊያደርሳቸው የቻለው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር ለሰዎች የሚሰጥህ መልዕክት በሰዎቹ ዘንድ የሚያስጠላህና ሊያስገድልህ እንኳን የሚችል ቢሆን ትናገረዋለህ ወይ? ሰዎች ለመስማት የሚፈልጉትን መልዕት ብቻ ሳይሆን ሊያስቆጣቸው የሚችለውንም መልዕክት ሳናስቀር መስጠት ከእግዚአብሄር ይጠበቅብናል።

# ጥናት ዘጠኝ ሉቃስ 5፡1-39

የጥናት ዓላማ፡- ለራሳቸው አንዳች አሳ ያልያዙት ጓደኞቻቸው መጥተው እነጴጥሮስን እንደረዱ ሁሉ፤ እኛም ሌሎች በአገልግሎታቸው ተሳክቶላቸው የእኛን እርዳታ በሚፈልጉበት ወቅት በደስታ ከጎናቸው ተሰልፈን የምናግዝ እንጂ በቅናት ተሞልተን ለአግልግሎታቸው እንቅፋትን የምናኖር ሰዎች እንዳንሆን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “በሌላ ጀልባ የነበሩት ባልንጀሮቻቸው መጥተው እንዲያግዟቸው በምልክት ጠሯቸው፤ እነርሱም መጥተው ሁለቱን ጀልባዎች በዓሳ ሞሏቸው፤ ጀልባዎቹም መስመጥ ጀመሩ።” ሉቃ 5፡7

1. ሉቃስ 5፡1-39 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-6 ላይ የሰፈረውን ታሪክ በማንበብ በራስህ ቋንቋ የተካሄደውን ነገር ለወገኖች ተናገር። በዚህ ምንባብ ውስጥ ስትመለከት የአሳ አጥማጆቹ ሞራል በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነበረ ትላለህ?
2. ቁ4-6ትን ስናነብ ኢየሱስ እነጴጥሮስን ምን እንዲያደርጉ ነው ትዕዛዝ የሚሰጣቸው? በዚህ ስፍራ ላይ ኢየሱስ ለነዚህ ሰዎች የመከረው ምክር ወይም የሰጠው ትዕዛዝ ስሜት የማይሰጠው በምን ምክንያት ነው?
3. ቁ6-10 ላይ ኢየሱስ እንደነገራቸው ባደረጉ ጊዜ የሆነው ነገር አንድ በአንድ ለወገኖች አስረዳ። በዚህ ሰዓት ኢየሱስን በመታዘዝ ምክንያት በሆነው ነገር የጴጥሮስ ምላሽ ምን ነበረ? ኢየሱስ ተአምራት አድርጎ ሰዎችን በማስደነቅ ብቻ ነገሩን ሊዘጋው ስላልፈለገ ለጴጥሮስ የሰጠው ትምህርት ምን ነበረ? አንተስ አዕምሮህ ለመቀበል ቢያስቸግረውም እንኳን ኢየሱስ የተናገረውን ነገር በእምነት ለመፈጸም ምን ያህል ዝግጁ ነህ?
4. ጴጥሮስ ወደፊት ሰዎችን ማጥመድ በሚጀምርበት ጊዜ ይህ ዛሬ የሆነው ነገር ትምህርት ሊሆነው የሚችለው በምን መንገድ ነው? በቁ12-13 ላይ የምንመለከተው ሰው የኢየሱስን ፈውስ በተመለከተ እርግጠኛ የሆነው አንድ ነገር ምን ነበረ? ይኸንንው ሰው መልሰን ስንመለከተው እርግጠኛ ሊሆን ያልቻለውና ኢየሱስ ማረጋገጥ የነበረበት አንድ ነገርስ ምን ነበረ?
5. ቁ14-16ትን ስንመለከት ኢየሱስ እጅግ ሥራ በበዛበት ወቅት እንኳን ማቋረጥ የማይፈልገው ነገር ምን እናያለን? ቁ17- 26ትን ስናነብ፤ በተለይም ቁ20 ላይ ኢየሱስን ለፈውስ ያነሳሳው የማንኛቸው እምነት ነው፣ የበሽተኛው ወይስ የጓደኞቹን? በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሱስን ተቃዋሚዎች ያበሳጨውና ጥያቄ የፈጠረባቸው ነገር ምንድነው? ሃጥያትን ማስተሰረይ መቻሉ የሚያረጋግጠው አንድ ነገር ምንድነው?
6. ቁ27-32 ላይ ለፈሪሳውያኑና ለጻህፍቱ ሰለኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ጥያቄ የፈጠረባቸው ነገር ምንድነው? ከኢየሱስ አመላለስ ስንመለከት “በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም” ሲል ፈሪሳውያኑን እንደምንድነው ያቀረባቸው? ይህ ማለት እውነት እነዚህ ሰዎች ጤነኞች ናቸው ማለት ነው ወይ? አስረዳ።
7. ቁ33-39 የኢየሱስ ጠላቶች ጥያቄአቸው አያበቃም። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥስ ለኢየሱስ የቀረበለት የነዚህ ሰዎች ጥያቄ ምን ነበረ? ለጥያቄአቸው የኢየሱስ መልስ ምን የሚል ነበረ? ከመልሱ ማለትም ከቁ35 ስንመለከት እንደኢየሱስ ተከታዮች እርሱ ከሄደ በኋላ የሚጠበቅባቸው ምን ነገር ይታይሃል?
8. መለስ ብለን በቁ7 ላይ የምናያቸው የእነጴጥሮስ ጓደኞች እዚያው ከእነርሱ ጋራ ሲለፉ አድረው ባዶውን መረባቸውን ሲያጥቡ እንደነበረ በቁ2 ላይ እናነባለን። እነጴጥሮስ መረባቸው ሞልቶ ጓደኞቻቸውን እርዳታ ሲጠይቁ ጓደኞቻቸው ለመርዳት የነበራቸው ፈቃደኛነት ምን ይምስል ነበረ? ያለምንም ማንገራገር ለእርዳታ መሄዳቸው ምን ሊያስተምረን ይችላል? አንተስ፣ ለሌሎች ሲሳካላቸውና የሚፈልጉትን ሲያገኙ ምን ዓይነት ስሜት ነው የሚሰማህ? እግዚአብሄር የሌሎችን ህይወት፣ አገልግሎት ወይም ቤተ ክርስትያን በተለያየ ነገር ሲባርክ፤ የደስታ ስሜት እንጂ በቅናት ተነስተን የምናደርገው ነገር እንዳይኖር ልንጠነቀቅ ይገባናል።

# ጥናት አሥር ሉቃስ 6፡1-26

የጥናት ዓላማ፡- ፈሪሳውያኑ ከኢየሱስ ትምህርትና ድርጊት ስህተት ፍለጋ በምኩራብ እንደተገኙ ሁሉ፤ ዛሬም በቤተ ክርስትያን እግዚአብሄርን ለማምለክና ከእርሱ ለመማር የሚመጡ እንዳሉ ሁሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ የሚካሄደውን ለመተቸት የሚገኙ ስላሉ፤ እኛም ወደ እግዚአብሄር ቤት ስንሄድ ምን ዓይነት ልብ ይዘን እንደምንሄድ ዘወትር ራሳችንን መመርመር እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ጻህፍትና ፈሪሳውያንም ሊከሱት ምክንያት በመፈለግ፤ ይፈውሰው እንደሆነ ለማየት ይጠባበቁት ነበር።" ሉቃ 6፡7

1. ሉቃስ 6፡1-26 በአንድነት ይነበብ። ሉቃስ በዚህ በቁ1 ላይ ደቀ መዛሙርት በማለት የሚናገረው ስለ አሥራ ሁለቱ ነው ወይስ ሌሎችንም ተከታዮቹን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ትላለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ። በቁ1-2 ላይ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በፈሪሳውያን የተከሰሱት እሸት ቀጥፈው በመብላታቸው ነው በሚለው አነጋገር ትስማማለህ ወይ? አይደለም ካልክ ግን የፈሪሳውያን የክስ ምክንያት ምን እንደነበረ ተናገር።
2. ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ እሸቱን ቀጥፈው በመብላታቸው በእግዚአብሄር ፊት ሃጥያት እንዳላደረጉ ለማስረዳት ለፈሪሳውያን በቁ3-5 ላይ የሰጣቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። በተለይ ኢየሱስ በቁ5 ላይ "የሰው ልጅ ለሰንበት ጌታዋ ነው።" በማለት የተናገረውን አነጋገር አንተ የሚገባህና የምትረዳው እንዴት ነው?
3. ቁ6-8 በተለይም ቁ6ትን ስንመለከት ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራብ ውስጥ የተገኘበት ዋነኛው ምክንያቱ ለምን ነበረ? ከእነዚህ ቁጥሮች እንደምንረዳው ጻህፍትና ፈሪሳውያኑስ በቤተ መቅደው ውስጥ የመገኘታቸው ዋነኛ ምክንያት ለምን እንደነበረ ነው የምንረዳው?
4. በቁ9-11 ላይ ኢየሱስ ሊከሱት ተዘጋጅተው ለመጡት ሰዎች ላቀረበላቸው ጥያቄ መልሳቸው ምን ነበረ? ኢየሱስ ለጻህፍቱና ለፈሪሳውያኑ ያቀረበውን ጥያቄ ለመመለስ ከባድና አስቸጋሪ የሚሆንባቸው ምክንያት ለምንድነው ትላለህ? ኢየሱስ ለጥያቄው መልስ እስኪያገኝ ሳይጠብቅ ሥራውን መስራት እንደቀጠለና ታማሚውን ሰው እንደፈወሰ እንመለከታለን። የሰውየውን መፈወስ በተመለከቱ ጊዜ ለክስ የመጡት ሰዎች የተሰማቸውን ስሜትና የወሰዱትን እርምጃ ተናገር።
5. ቁ12-16 ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ለመምረጥ ያደረገው ዋነኛ ቅድመ ዝግጅት ምን ነበረ? ይህንን ያህል ጊዜ በጸሎት ከአባቱ ጋራ ካሳለፈ በኋላ ባደረገው ምርጫ ውስጥ ካስገባቸው ሰዎች መካከል እንደ አንተ አመለካከት ቢሆን ከቁጥር መግባት አልነበረበትም የምትለው አንድ ሰው ተናገር። በአንጻሩ ደግሞ ከተመረጡት ሰዎች ውስጥ ባይኖር ኖሮ ለቤተ ክርስትያን ብዙ ነገር ያጎድል ነበር የምትለውንና ምክንያትህን ጭምር ተናገር።
6. ቁ17 ላይ "ኢየሱስም አብሯቸው ከተራራው ወርዶ ደልዳላ ቦታ ላይ ቆመ።" በዚህ ሥፍራ ላይ አብሯቸው በማለት የሚናገረው ስለነማን ነው? በቁ17-19 ውስጥ ተሰብስበው የሚገኙት ሰዎች ማን ማን እንደሆኑ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ ሰዎች ወደዚህ ስለመጡበት ምክንያት ይህ ክፍል ምን ይነግረናል?
7. በቁ17-19 ላይ ተሰብስበው የምንመለከተውን ቁጥሩ እጅግ ብዙ የሆነውን ህዝብ ኢየሱስ በቁ20-26 ላይ በስንት ከፍሏቸው እንመለከታለን? ምንና ምን እንደሆነ ተናገር። ኢየሱስ ድህነትን፣ ረሃብን፣ ለቅሶንና ነቀፋን እንደ ብጽዕና አድርጎ በማስቀመጥ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሃብታምነትን፣ ጥጋብን፣ ሳቅንና መልካም ንግግርን ወዮላችሁ በሚል አስቀምጦታል። ኢየሱስ ይህንን ሲል ሳንቲም በኪሱ ያልተገኘ፣ ምግብ በሆዱ ያልገባና እንባ ከአይኑ የማይጠፋ ሰው እግዚአብሄር ይወደዋል፤ በአንጻሩ ደግሞ ሌሎቹን ከዚህ የተቃረኑትን ሰዎች አይፈልግም ለማለት ነው ወይስ ኢየሱስ በዚህ ክፍል በአጠቃላይ ምን ለማለት እንደፈለገ አስረዳ።
8. በቁ6-11 ያለው ነገር የተካሄደበት ሥፍራውና፤ ፈሪሳውያን የተገኙበት አስተሳሰብ የሚጋጨው ለምንድነው? አንተስ ወደ እግዚአብሄር ቤት የራስህን አጀንዳ ለማካሄድ የተመላለስክበት ጊዜ አለ ወይ? ወደ እግዚአብሄር ቤት ስንሄድ ሊኖረን የሚገባው አንድና ዋነኛ ዓላማ፤ እግዚአብሄርን ማምለክና እርሱን ለማክበር እንጂ በዚያ የሚካሄደውን ነገር ለመተቸት መሆን የለበትም።

# ጥናት አሥራ አንድ ሉቃስ 6፡27-49

የጥናት ዓላማ፡- ሕይወታችን የእግዚአብሄርን ቃል በመስማት ብቻ ሳይሆን ሰምቶ በመታዘዝ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤ ማናቸውም ዓይነት ከባድ መከራና ፈተና በሚነሳ ሰዓት ሳንናወጥ መቆም የምንችል ሰዎች ለመሆን የሚያስችለን እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ወደ እኔ የሚመጣ፣ ቃሌንም ሰምቶ የሚፈጽም…፤ ቤት ለመስራት አጥልቆ የቆፈረና በዓለት ላይ መሰረቱን የመሰረተ ሰው ይመስላል፤ ጎርፍ በመጣ ጊዜ የውሃ ሙላት ያን ቤት ገፋው በመገባ ስለታነጸም ሊያነቃንቀው አልቻለም።" ሉቃ 6፡47-48

1. ሉቃስ 6፡27-49 በአንድነት ይነበብ። ኢየሱስ ቁ27 ላይ ንግግሩን ሲጀምር "ለእናንተ ለምትሰሙ" በማለት የተናገረውን በቁ6-7 ከሚታየው ሁኔታ ጋራ በማነጻጸር ስንገመግመው ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? በቁ27 እና 28 ላይ ስብከቱን እየሰሙ የነበሩት ወይም ደግሞ ዛሬም ቢሆን የእርሱን ቃል የሚሰሙት ተከታዮቹ እነርሱ ሊቆጣጠሯቸው የማይችሏቸው ሶስት ነገሮችና፤ እነርሱ ሊቆጣጠሯቸው የሚችሏቸው ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. በቁ32-34 ላይ ቢያንስ ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ የተጠየቀ ጥያቄ አለ፤ ያ ጥያቄ ምን እንደሆነ ተናገር። በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የምንመለከተው፤ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ያስቀመጠውን መለኪያና ሚዛን ከማን ጋራ ሲያነጻጽረው ነው የምናገኘው? ስለዚህ በነዚህ ቁጥሮች ኢየሱስ የተናገራቸውን ሶስቱን የማነጻጸሪያ አረፍተ ነገሮች በመመልከት፤ ለተከታዮቹ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋነኛው ትምህርቱ ምንድነው ማለት ይቻላል?
3. በቁ35-36 ላይ ጠላት መውደድ፣ መልካም ማድረግና ክፍያ ሳይጠብቁ በማበደር የሚገኙት ሁለት ጥቅሞች ወይም ትርፎች ምንና ምንድናቸው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የልዑል ልጆች እንዲለማመዱቸው የተነገሩትና የልዑል እግዚአብሄር ባህርያት ሆነው የተነገሩት ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ውስጥ በቁ37 ላይ "አትፍረዱ አይፈረድባችሁም…" በማለት ሲያስተምር እንመለከታለን፤ በዮሐ 7፡24 ላይ ደግሞ እርሱ ራሱ "የሰውን ፊት በማየት መፍረድ ትታችሁ ቅን ፍርድ ፍረዱ" በማለት ሲናገራቸው እናነባለን። እነዚህ ሁለት የኢየሱስ አነጋገሮች በትክክለኛው መንገድ ከተተረጎሙ የማይጋጩና ሁለቱም ትክክለኛ ትምህርቶች መሆናቸውን ለማስረዳት ሞክር።
5. በቁ39-40 ላይ መሪና ተመሪ፤ አስተማሪና ተማሪን እንመለከታለን። ከኢየሱስ አነጋገር ስንረዳ፤ ሌላውን እውር እመራለሁ ከሚል ሰው የሚጠበቅበት አንድ ነገር ምንድነው ይለናል? በዚሁ አንጻር ስንመለከተው፤ ሌላውን አስተምራለሁ የሚል ሰው ካለ ደግሞ ከዚያ አስተማሪ የሚጠበቀው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ከነዚህ ሁለት ሃሳቦች በመነሳት እኛ ለራሳችን መውሰድ የምንችለው ትምህርት ምንድነው?
6. ቁ41-42ትን ስናነብ በሌሎች ሰዎች ውስጥ የምናየውን ስህተት ለማረም ከመነሳታችን አስቀድመን ማድረግ የሚገባንን ነገር ኢየሱስ ይናገራል፤ ይህ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ምንድነው? አስቀድሞ በራስ ውስጥ ያለውን ምሰሶ ማስወገድ ለምንድነው በሰዎች ውስጥ ያለውን ስህተት ለመጠቆም የሚረዳው? በራሱ ህይወት ውስጥ ትልቅ የሆነ የሚታይ ስህተት ወይም ምሰሶ ተጋድሞ እያለ የሌላውን ጉድፍ ለማንሳየት የሚሞክረውን ሰው ኢየሱስ ምን በማለት ነው የሚጠራው?
7. ኢየሱስ በቁ43-44 ላይ ያስተማረውን ሃሳብ ስንመለከት፤ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የምናገኘው አንድ ቃል ምን የሚል ነው? የተለያዩ የዛፍ ዓይነቶችን በመጥቀስ ኢየሱስ ሊያስተምር የፈለገው ዋነኛና ማጠቃለያ ሃሳብ አድርጎ ያቀረበው ነገር ምንድነው?
8. በቁ46-49 ላይ ወደ ኢየሱስ መጥተው ትምህርቱን የሚሰሙትን ሰዎች ኢየሱስ በስንት ዓይነት ሲከፍላቸው ነው የምንመለከተው? አከፋፈላቸው ምንና ምን ብሎ እንደከፋፈላቸው ተናገር።
9. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የኢየሱስን ትምህርት ሰምቶ በመታዘዝና ባለመታዘዝ መካከል ስላለው ልዩነት የሚነግረን ሃሳብ ምንድነው? አንተስ ህይወትህን ስትመረምረው የተመሰረተው በዓፈር ላይ ይሆን ወይስ በዓለት ላይ? ህይወታችን በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳይናወጥና ጸንቶ ለመቆም ካስፈለገ፤ በእግዚአብሄር ቃል ላይ መመስረትና መቆም አማራጭ የሌለው እውነት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

# ጥናት አሥራ ሁለት ሉቃስ 7:1-50

የጥናት ዓላማ:- ምንም እንኳን ደህንነታችንን ለማግኘት ወይም ለማረጋገጥ ለኢየሱስ ማድረግ የሚኖርብን ነገር ባይኖርም፤ እርሱ ላደረገልን ታላቅ መስዋእትነት ጥልቅ ፍቅራችንን ለመግለጥ የምንችልበት አንደኛው መንገድ አገልግሎታችን እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ:- "…አንተ ለእግሬ ውሃ አላቀረብክልኝም፣ እርሷ ግን እግሬን በእንባዋ እያራሰች በጠጉርዋ አበሰች፤ አንተ ኩኖ አልሳምከኝም፣ እርሷ ግን ከገባሁ ጀምራ እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም፤ አንተ ራሴን በዘይት አልቀባህም፣ እርሷ ግን እግሬን ሽቶ ቀባች፤ ስለዚህ እልሃለሁ፤ እጅግ ወዳለችና ብዙው ሃጥያቷ ተሰርዮላታል።" ሉቃስ 7፡44-47

1. ሉቃስ 7:1-50 በአንድነት ይነበብ። በቁ1- 5 ውስጥ የምንመለከተ የመቶ አለቃ ከአገልጋዩ ጋራ ስለነበረው ግንኙነት ምን እንረዳለን? ይህ ሰው አገልጋዩ ፈውስ እንዲያገኝ ወደ ኢየሱስ ለመቅረብ የተጠቀመበት መንገድ ምን ነበረ? ወደ ኢየሱስ ተልከው የሄዱት መልዕክተኞች ይህ ሰው የኢየሱስን እርዳታ ማግኘት የሚገባው ሰው እንደሆነ ለማረጋገጥ የተጠቀሙባቸው ሁለቱ ምክንያቶች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. ቁ6-10 ላይ ስናነብ ይህ የመቶ ዓለቃ ራሱን ከኢየሱስ ጋራ በማነጻጸር ስለራሱና ደግሞም ስለ ኢየሱስ የተረዳው ነገር ምን ታያለህ? ይህ ሰው በኢየሱስና በራሱ መካከል ያለውን ወይም ደግሞ ኢየሱስ የታመመውን ባሪያውን ለመፈወስ የግድ ወደ እርሱ ቤት መግባት እንደማይኖርበት ለማስረዳት የተጠቀመበት ምሳሌ ምን ነበረ? በቁ9 ላይ ላይ የዚህ ሰው እምነት ኢየሱስን እንዳስገረመው እናነባለን፤ ኢየሱስን ያስገረመው ዋነኛ ብለህ የምታስበው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር። አንተስ እምነትህ ኢየሱስን ለማስገረም እስከሚደርስ ድረስ እንዲያድግ የምታደርገው ነገር አለ ወይ? 2ተሰ 1፡3
3. በቁ11-17 ላይ የምናነበውን ታሪክ በቁ1-10 ላይ ከተመለከትነው ታሪክ ጋራ በማስተያየት፤ በነዚህ ሁለት ታሪኮች ውስጥ ኢየሱስ ያደረጋቸውን ሁለት ተአምራቶች እንመለከታለን። በነዚህ ሁለት ተአምራቶች ውስጥ ማየት የምንችላቸውን ልዩነቶች በመዘርዘር ለመናገር ሞክር። እነዚህን ሁለት ከኢየሱስ ተአምራት የተቀበሉትን ሰዎች ጎን ለጎን በማነጻጸር ስታይ፤ ከእግዚአብሄር አንዳች ነገርን ለመቀበል በህብረተሰብ ውስጥ ያለን ሥፍራ ምን ያህል ሚና ይጫወታል ብለህ ታምናለህ? አስረዳ።
4. ይህ በነዚህ ቁጥሮች ማለትም በቁ11-17 ላይ የምናነበው ኢየሱስ በናይን ከተማ ውስጥ ያደረገው ተአምር ቢያንስ አራት ውጤቶች እንዳስገኘ ከቁ17 ላይ ማየት እንችላለን፤ እነዚህ አራት ነገሮች ምን ምንድናቸው? ይህች አንድ ልጇን ያጣች ሴት በሃዘኗ ተሳታፊዎች የሆኑ ብዙ ሰዎች እንመለከታለን፤ የሴትየዋ ሁኔታ ግን መቀየር የቻለው መቼ ነበረ? አንተስ ብዙ ወዳጅና ዘመድ በአካባቢህ እያሉህ ያለህበትን ሁኔታ ግን ለመቀየር ኢየሱስ ብቻ ያስፈለገበትን ጊዜ ታስታውሳለህ ወይ?
5. በቁ18-23 ያለው የመጥምቁ ዮሐንስ ታሪክ በማቴ 11:2-6 ላይም ተጽፎ እናገኘዋለን። እነዚህን ሁለት ክፍሎች በመመልከት መጥምቁ ዮሐንስን አስቀድሞ እርሱ ራሱ የመሰከረለትን ኢየሱስ ዛሬ የዚህ ዓይነት ጥያቄ ለመጠየቅ ያደረሰው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? ቁ31-35 ላይ ትውልዱ ምን እንደሚመስል ኢየሱስ ከተናገረው አነጋገሩ ስትመለከት፤ ለነዚያ ሰዎች ሊያስተላልፈው የፈለገው ምልዕክት ምን ነበረ?
6. ኢየሱስ በአብዛኛው አገልግሎቱ ፈሪሳውያንን ሲነቅፍና ስህተታቸውን ለህዝብ አጉልቶ ሲያሳይ እናያለን፤ ሆኖም በዚህ ክፍል በቁ36 ላይ ስናነብ የፈሪሳውያኑን ግብዣ ተቀብሎ እንደሄደ እንመለከታለን። ከዚህ ከኢየሱስ ድርጊት ምን መማር እንችላለን?
7. ቁ36-38 ላይ ኢየሱስን ፍለጋ ወደ ፈሪሳዊው ቤት ስለመጣችው ሴት ማንነት የተነገርው ነገር ምንድነው? ይህች ሴት ወደ ፈሪሳዊው ቤት መጥታ ስታደርግ የምናነባቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ተናገር።
8. ፈሪሳዊው ይህች ሴት ለኢየሱስ ያደረገችውን ነገሮች ሁሉ ተመልክቶ ለተናገረው ነገር መልስ ለመስጠት ከቁ40 ጀምሮ ያለውን ነገር ተናገረ ቢባል ትክክለኛ አባባል ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ። ይህ ሰው ምንም ዓይነት ነገር ከአንደበቱ ሳያወጣ ኢየሱስ በልቡ ያለውን አውቆ መልስ መስጠት መቻሉ የሚያረጋግጠው ነገር ምንድነው? ከስምዖን አነጋገር ስትመለከት፤ ይህ ሁኔታ ለእርሱ እንዳረጋገጠለት አድርጎ ያሰበው አንድ እውነት ምን ነበረ?
9. ስምዖንንና ሴቲቱን በማነጻጸር በቁ44-47 ኢየሱስ ከተናገረው ስንመለከት የፍቅር መግለጫ ሆኖ የቀረበው አንድ ነገር ምንድነው? አንተስ ኢየሱስን ለመውደድህ ማረጋገጫ ምን በማድረግ ላይ ትገኛለህ? ጌታ ላደረገልን ነገር ፍቅራችንን ለመግለጽ የተሰጠን አንድ ነገር እርሱን ማገልገል እንደሆነ መዘንጋት የለብንም።

# ጥናት አሥራ ሶስት ሉቃስ 8፡1-56

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ እንኳን በልባቸው ውስጥ የወንጌልን ዘር የሚዘራባቸው ሰዎች ሁሉም ሙቶ በሙቶ ፍሬ የሚያፈሩ እንዳልሆኑ ከተመለከትን፤ በእኛ አገልግሎትም ሰዎች መልዕክታችንን ለመቀበል ፈቃደኞች ባይሆኑ እንኳን የራሳችን ጥፋት አድርገን ተስፋ መቁረጥ እንደማይኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስ ውሃ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን እግዚአብሄር ነው።" 1ኛ ቆሮ 3፡6

1. ሉቃስ 8፡1-56 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ባለው ምንባብ ውስጥ የምትመለከታቸውን ሰዎች ሁሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር። ኢየሱስ በቁ5 ጀምሮ የተናገረውን የዘሪውን ምሳሌ ለመስማት የተሰበሰበው ሰው ቁጥር በጣም ብዙ መሆኑን ሊጠቁሙን የሚችሉትን አንዳንድ ቃላት በመጥቀስ ተናገር።
2. በቁ5-15 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃሉን የሚሰሙትን ሰዎች በስንት ዓይነት ነው ከፍሏቸው የምናገኘው? እነዚህ ኢየሱስን የሰሙት ሰዎች ሁሉ የሚመሳሰሉበት አንድ የጋራ ነገር አላቸው፤ ይህ ለሁሉም የጋራ የሆነው ነገር ምንድነው? በአንተ አመለካከት እነዚህን ሁሉ ሰሚዎች አንደኛውን ከሌላኛው የሚለየው አንድ ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
3. በቁ19-21 ላይ ከምናነበው ሃሳብ በመነሳት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል ወንድሞች እንዳሉት ነው የምንመለከተው? ኢየሱስ ቤተሰቦቹ ሊያዩት እንደሚፈልጉ ሲነገረው "እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሄርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው" በማለት መናገሩ፤ ለአማኝ ቤተሰብ የሚባል ነገር የለም ለማለት ፈልጎ ነው ወይ? ካልሆነስ ጌታችን ይህንን ዓይነት አነጋገር ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው ብለህ ታምናለህ?
4. በቁ22-25 ላይ የተጠየቁ ሁለት ጥያቄዎችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ናቸው? ደቀ መዛሙርቱ በፍርሃትና በመደነቅ እንደተሞሉ ቁ25 ይነግረናል። ደቀ መዛሙርቱን በፍርሃትና በመደነቅ እንዲሞሉ ያደረጋቸው ነገር የኢየሱስ ነፋሱንና ውሃውን ማዘዝ ነው ውይ? አስረዳ።
5. በቁ26-29 ላይ ስናነብ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢጋንንት ያደረበት ሰው እንደተገናኘው እናያለን። ከዚህ ክፍል ውስጥ ስለዚህ ሰው ማወቅ የምንችላቸውን ነገሮች በሙሉ በዝርዝር ተናገር። ያዕ 2፡19 ላይ የሚናገረው እውነት በዚህ ክፍል ውስጥ በተግባር ሲገለጥ የሚታየው በየትኛው ሃሳብ ውስጥ እንደሆነ ተናገር።
6. 30-37 ላይ ባለው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይጣን ላይ የበላይነት እንዳለው የሚያሳይ አንድ ክፍል ጥቀስ ብትባል የትኛውን ክፍል እንደምትጠቅስ ተናገር። ቁ35-37 ላይ የጌርጌሴኖን ሰዎች ያንን አስቸጋሪና በሰንሰለት እንኳን መቆጣጠር ያልተቻለውን ሰው ለብሶና ወደ ህሊናው ተመልሶ ሲያዩት ለራሳቸው የተሰማቸው ስሜትና ከዚህም የተነሳ በኢየሱስ ላይ የወሰዱት እርምጃ ምን ነበረ? ኢየሱስ ውጣልን ሲባል እሺ ብሎ መውጣቱ ለእኛ ምን የሚያስተምረን ነገር ይኖራል?
7. በቁ37 ላይ የጌርጌሴኖን ሰዎች ለኢየሱስ ባሳዩት አቀባበልና በቁ40 ላይ ኢየሱስ ባገኘው አቀባበል የምታየው ልዩነት ምንድነው? በቁ43-48 ላይ ይህች አስራ ሁለት ዓመታት ደም ይፈሳት የነበረች ሴት ታሪክ ይገኛል፤ መንካት ብሎ ኢየሱስ ለሚለው ነገር በጴጥሮስና በኢየሱስ የአመለካከት ልዩነት እንዳለ ቁ45 እና ቁ46 ያሳዩናል። በነዚህ ሁለት አመለካከቶች መሃል የምታየውን የትርጉም ወይም የአመለካከት ልዩነት ተናገር። አንተስ ኢየሱስን ከሚያጋፉት ወይስ ከሚነኩት መሃል ነህ?
8. እንደሰው አመለካከት ሲታይ፤ ይህች ደም ይፈሳት የነበረች ሴት በመሃል መምጣቷ ኢያኢሮስ ለሚባለው ሰው መልካም ነበረ ማለት የምንችልበትና በተቃራኒው ደግሞ መልካም አልነበረም ማለት የሚያስችሉን ነገሮች ምን እንደሆኑ ተናገር።
9. ወደ ቁ11-15 የተመለከትናቸው የእግዚአብሄር ቃል ተዘርቶባቸው በትክክል ፍሬ ያፈሩት ከአራቱ አንዱ ብቻ መሆናቸውን መረዳት፤ ለወደፊቱ የወንጌል አገልግሎታችን በምን መንገድ ይጠቅመናል ትላለህ? ወንጌልን ለሰዎች ተናግረህ ፍሬ ለማየት አለመቻልህ ተስፋ ያስቆረጠህ ጊዜ አለ ወይ? አንዳንዴ የወንጌልን እውነት በሰዎች ልብ ውስጥ ስትዘራ ፍሬውን ማየት ባትችልም እንኳን፤ የሚያሳድገው እግዚአብሄር ስለሆነ በእምነት መዘራትህን ቀጥል።

# ጥናት አሥራ አራት ሉቃስ 9፡1-62

የጥናት ዓላማ፡- ሰዎች ወደ ጌታ የሱስ ለመምጣት እርምጃ ለመውሰድ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት፤ የነፍሳችን ጠላት የሆነው ዲያቢሎስ ባለው በሌለው ሃይሉ በመጠቀም ተስፋ ቆርጠን ከደህንነት መንገድ ፊታችንን ወደ ቀድሞው ኑሯችን እንድንመልስ እንደሚሞክር ለማስገንዘብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ልጁ በመምጣት ላይ ሳለም ጋኔኑ መሬት ላይ ጥሎ አንፈራገጠው፤ ኢየሱስ ግን ርኩሱን መንፈስ ገስጾ ልጁን ፈወሰው፤ ለአባቱም መልሶ ሰጠው።" ሉቃ 9፡42

1. ሉቃስ 9፡1-62 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-6 ትን ስንመለከት፤ በተለይም ቁ1ና2 ላይ ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሲልክ ከእርሱ የተቀበሏቸው ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በነዚህ ስድስት ቁጥሮች አነጋገር የሐዋርያቱ ዋነኛ ትልዕኮዎች ምን ምንድናቸው ማለት እንችላለን?
2. በቁ10-11 ላይ ስናነብ ኢየሱስ በዚያን ሰዓት ጊዜውን ማሳለፍ የፈለገው በምን ሁኔታ ይመስልሃል? ኢየሱስ ጊዜውን እርሱ ባሰበው መንገድ ማሳለፍ እንዳይችል የተገደደበት ምክንያት ምን ነበረ? በጊዜው ኢየሱስ ለራሱና ለሐዋርያቱ ያቀደው ፕሮግራም መዛባት ላይ ሳያተኩር በህዝቡ ፍላጎት ላይ በማተኮር ወንጌልን ሲሰብክላቸውና ፈውስ ለሚያስፈልጋቸውም ፈውስን ሲሰጥ ይታያል፤ ከዚህ ሁኔታ ለራሳችን ህይወት ልንማር የምንችለው እውነት ምንድነው?
3. በቁ18-21 ላይ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሁለት አይነት ጥያቄዎችን ሲያቀርብላቸው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን ነበሩ? ኢየሱስ በከተማው ስለእኔ ምን ይወራል የሚለውን ዜና ለመስማት ነው ወይስ ለምን ይመስልሃል እነዚህን ጥያቄዎች ለደቀመዛሙርቱ ማቅረብ የፈለገው? ኢየሱስ ከጠየቃቸው ሁለት ጥያቄዎች መሃል ለደቀመዛሙርቱ ህይወት ወሳኝነት ያለው የትኛው ጥያቄ ነው ትላለህ? ለምን?
4. ቁ22-27ን በተለይም ደግሞ ቁ22ትን ስናነብ ኢየሱስ እንደሚያልፍባቸው የተነገሩት አራት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር። ከእነዚህ አራት ነገሮች ውስጥ ለሶስቱ መፈጸም ምክንያት የሚሆኑ አራት አይነት ሰዎች ተጠቅሰዋል፤ እነዚህ አራት አይነት ሰዎች እነማን ናቸው? ከቁ23-27 ላይ ኢየሱስ የተናገረው ነገር፤ ቀደም ብሎ በቁ22 ላይ ከተናገረው ስለራሱ ከተናገራቸው ሃሳብ ጋራ ምን የሚዛመድበት መንገድ ሊኖር እንደሚችል አስረዳ።
5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቁ28-36 ላይ ስናነብ ሶስቱን ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ወደ ተራራ የወጣበት ምክንያት ለምን ነበረ? እዚህ ተራራ ላይ በቆዩበት ሰዓት እርሱ በጸሎትና በልዩ ልምምድ ውስጥ በነበረበት ሰዓት አብሮ የወሰዳቸው ደቀመዛሙርቱ በምን ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ተናገር። ኢየሱስና ሶስቱ ደቀመዛሙርት ያ ሁሉ ክብር የታየበትን ተራራ ትተው ወደታች እንደወረዱና የሚጠብቃቸውን የእለት እለት ተግባራቸውን ማከናወን እንደጀመሩ እናያለን፤ እኛስ ከዚህ መማር የምንችለው ነገር ምንድነው ትላለህ?
6. በቁ22 ላይ እንደሚገደል፣ በቁ31 ላይ ከሙሴና ከኤልያስ ጋራ ሰለሞቱ ማውራቱ፣ በቁ44 ላይ ደግሞ አልፎ እንደሚሰጥ በመናገር ለደቀመዛሙርቱ ይናገራል። ለምንድነው ኢየሱስ ስለሞቱ እንዲገባቸው፣ እንዳይረሱትና ሁልጊዜ እንዲያስታውሱት የሚፈልግበት ምክንያት ለምንድነው? ቁ44 ላይ ሞቱን አስመልክቶ ያለውን ነገር በልባቸው እንዲያኖሩ እየነገራቸው፤ ወረድ ብሎ በቁ 46 ላይ የሚሆነውን ስንመለከት ደቀመዛሙርቱ ስለሚገኙበት መንፈሳዊ ሁኔታ ምን መናገር እንችላለን?
7. በቁ46-50 ላይ በደቀ መዛሙርቱ መካከል የእርስ በርስ መወያያና ጥያቄ የነበረው ነገር ምን ነበረ? ለዚህ ክርክራቸው ወይም ጥያቄአቸው የኢየሱስ አጭር መልስ ምን ነበረ? በዮሐንስ አመለካከት አንድ ሰው አጋንንት ለማስወጣት ወይም ተአምራትን ለማድረግ የሚጠበቅበት ነገር ምን ነበረ?
8. በቁ57-62 ላይ የመጀመሪያው ሰውዬ ኢየሱስን ለመከተል ያለውን ብርቱ ፈቃደኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመበት አነጋገር ምን የሚል ነው? ኢየሱስ ደግሞ በበኩሉ ሰውየው አውቆ እንዲገባበት የፈለገው ነገር ምን ነበረ? ቀጥሎ ያሉት ሁለቱ ሰዎች ኢየሱስን ላለመከተል ያቀረቡት ምክንያታቸው የሚመሳሰለው በምን መንገድ ነው ብለህ ታምናለህ?
9. ቁ42ትን መለስ ብለን ስናይ ለዚያችን ሰዓት ጤና የነበረው ልጅ ወደየሱስ መምጣት በጀመረበት ወቅት የተከሰተው ነገር ምን ነበረ? ይህ ሁኔታ በአባትየው ውስጥ ሊፈጥር የሚችለው ነገር ምን ይመስልሃል? ወደ ኢየሱስ ስመጣ መከራዬ ባሰብኝ የሚሉ ሰዎች ገጥመውህ ያውቃሉ ወይ? ሰይጣን ያለ የሌለ ሃይሉን ተጠቅሞ ወደ ኢየሱስ ከመምጣት ተስፋ ሊያስቆርጥ መሞከሩን እንደማያቆም ልትረዳ ያስፈልግሃል።

# ጥናት አሥራ አምስት ሉቃስ 10፡1-42

የጥናት ዓላማ፡- ከወገኖች ቤት ስንገባ ጥቂት ጊዜ ወስደን የእግዚአብሄርን ቃልና፤ እግዚአብሄር በህይወታችን እየሰራ ያለውን ነገር መከፋፈል ክተለያየ አሉዋልታና ከማይረባ ነገር ከመጠበቅ አልፎ ህይወታችንም የሚገነባበት መንገድ ስለሆነ፤ የጌታችንን ምሳሌ መከተል ይበጀናል።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “እርሷም ማርያም የተባለች እህት ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ እግር ስር ተቀምጣ ነበር።” ሉቃ 10፡39

1. ሉቃስ 10፡1-42 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ጌታ ሌሎች ሰባ ሁለት ሰዎችን መርጦ ሲሾም እንመለከታለን። እነዚህ ሰዎች እንዲያደርጉ የሚያዛቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ምን ምንድናቸው? እንደ በጎች በተኩላዎች መሃል መላክ፣ ኮረጆና ከረጢት የመሳሰሉትን አለመያዝና፣ ለማንም ሰላምታ ሳይሰጡ መሄድ የሚሉትን ነገሮችን በመናገር ስለተልዕኳቸው ሊያስገነዝባቸው የፈለገው ሶስት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. ቁ5-7 ወደማንኛውም ቤት ሲገቡ ማድረግ ያለባቸውንና ቁ8-11 ደግሞ ወደ ማንኛውም ከተማ ሲገቡ ማድረግ ያለባቸውን ይናገራል። እነዚህን ቁጥሮች ስናነብ እነዚህ ሰዎች በሄዱበት ሁሉ ሊገጥሟቸው የሚችሉት ስንት አይነት ሰዎችን ትመለከታለህ? እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር። በጉዟቸው የተለያዩ ሰዎች እንደሚገጥሟቸው ቢያውቅም እንኳን ኢየሱስ ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም ለሁሉም እንዲደርሳቸው የፈለገው መልዕክት ምን ነበረ? ሰዎች ሁሉ መልዕክታችንን ይቀበላሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ሲሆን፤ የእኛ ሃላፊነት ግን ለሚቁበሉም ሆነ ለማይቀበሉ የክርስቶስን ወንጌል መናገር ነው።
3. ከጌታ ኢየሱስ አነጋገር እንደምንረዳው ከሆነ ቁ16-17 ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ማስተላለፍ የፈለገው ሃሳብ ምን ነበረ? በቁ17-20 ላይ ስናይ ሰባ ሁለቱ ሰዎች ደስታቸው ማድረግ በቻሉት ነገር ላይ ሲሆን፤ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ የደስታቸው ዋነኛ መሰረት አድርጎ የሚነግራቸው ነገር ምንድነው? አንተስ የደስታህ መሰረቱ ለእግዚአብሄር እየሰራህ ባለኸው ነገር ላይ ነው ወይስ እግዚአብሄር ለአንተ በሰራው ነገር ላይ?
4. ቁ21-24 ላይ ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ደስ ያሰኘውና በመንፈስ ቅዱስ ሃሴትን እንዲያደርግ ያደረገው ነገር ምን ነበረ? “…እናንተ የምታዩትን ለማየት ፈልገው አላዩም፤ የምትሰሙትንም ለመስማት ፈልገው አልሰሙም።” በማለት ኢየሱስ በቁ24 ላይ የተነገረው ነገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
5. በቁ25 ላይ የምንመለከተው ሰው ኢየሱስን የጠየቀው ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ይህ ሰው የነበረውን የእግዚአብሄር ቃል እውቀት ለምን ዓይነት ነገር ሲጠቀምበት ነው የምናገኘው? አንተስ በውስጥህ የሞላውን የእግዚአብሄር ቃል ሰዎችን በክርክር ለመርቻ ወይስ ሌሎችን ለመገንቢያ ትጠቀምበታለህ?
6. ኢየሱስ የህግ አዋቂው የጠየቀውን ጥያቄ በቀጥተኛ መንገድ እንዳልመለሰለት እናያለን፤ ታዲያ ኢየሱስ ጥያቄውን በምን ዓይነት መንገድ ነው የመለሰለት? ቁ26-29ን ስታነብ ይህ ሰው እውነትም እውነትን እየፈለገ ያለ ሰው እንዳልነበረ የሚያስገነዝበን ምን ነገር ትመለከታለህ? ይህ የህግ አዋቂ ኢየሱስን የጠየቀው ሁለተኛ ጥያቄ ምን የሚል ነበረ?
7. ቁ30-37ትን ስናነብ ኢየሱስ ሰውየው ለጠየቀው ሁለተኛ ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ሰጥቶታል ወይ? ለምን ይመስልሃል ጌታ ኢየሱስ ለዚህ ሰው ቀጥተኛ የሆነ መልስ ላለመስጠት የወሰነው? ቁ37 ላይ ኢየሱስ ምሳሌውን ሲያጠቃልል የህግ አዋቂው የጠበቀውን አይነት መልስ የሰጠው ይመስልሃል ወይ? አስረዳ።
8. በቁ38-42 ላይ የሰፈረው ታሪክ በተነበበ ቁጥር ትኩረቱ በአብዛኛው በማርያም ወይም በማርታ ላይ እንደሚሆን እናውቃለን። ዛሬ ትኩረታችንን በኢየሱስ ላይ ብናደርግ፤ በነዚህ ሴቶች ቤት ገብቶ ኢየሱስ ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? አንተስ ከወገኖች ጋራ ስትገናኝ ወይም ወደ ሰዎች ቤት ስትሄድ ከወገኖች ጋራ ቃሉን የምትካፈልበት ጊዜ ትወስዳለህ ወይ? ከወገኖች ጋራ በምንገናኝበት ወቅት ብዙ የሚደረጉ ነገሮች እንዳሉ ቢታወቅም እንኳን፤ ቃሉን ከፍቶ እግዚአብሄር ያስተማረንን መካፈል መለማመድ ለሁሉም በረከት እንደሚሆን አያጠራጥርም።

# ጥናት አሥራ ስድስት ሉቃስ 11፡1-54

የጥናት ዓላማ፡- እውነትን መናገር በእግዚአብሄር ዘንድ ደስ የሚያሰኝ በጎ ሲሆን፤ አብዛኛው ሰው ግን እውነትን መስማት የሚፈልገው እርሱ እስካልተነካ ወይም ስለርሱ በጎ እስከተነገረ ብቻ ሊሆን ስለሚችል፤ በተለይ ተግሳጽን ያዘለ እውነት ስንናገር ከምስጋና ይልቅ ጠንካራ ተቃውሞ ሊገጥመን እንደሚችል በማወቅ ማድረግ እንደሚገባን።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ኢየሱስ ከዚያ ከወጣ በኋላ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ክፉኛ ይቃወሙትና በጥያቄም ያዋክቡት ጀመር፡ ከአፉ በሚወጣውም ቃል ሊያጠምዱት ያደቡ ነበር።" ሉቃስ 11፡53-54

1. ሉቃስ 11፡1-54 በአንድነት ይነበብ። 1ኛ ተሰ 5፡17 ላይ "ሳታቋርጡ ጸልዩ" ይላል፤ በዚህ ክፍል ደግሞ በቁ1 ላይ ስናነብብ ኢየሱስ ፀሎቱን እንደጨረሰ ወይም እንዳቋረጠ እንመለከታለን። በ1ኛ ተሰ 5፡17 ላይ የታዘዝነው ትዕዛዝ ያለማቋረጥ ተንበርክኮ መዋል ማለት ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል ብለህ እንደምታምን አስረዳ። በቁ1-4 ባለው ክፍል ውስጥ በተለይ አንደኛው ደቀመዝሙር ስለፀሎት ለመማር ፍላጎት ያሳደረበት ሁኔታ ምን ነበረ? ሉቃ 6፡28 ላይ እንዲፀልዩ ተናግሯቸው እንዴት እንደሚፀልዩ ሳይጠይቁት አሁን እርሱ ሲያደርገው ሲያዩ ፀሎት እንዲያስተምራቸው መጠየቃቸው ምን ያስተምረናል?
2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከቁ5-13 ባለው ክፍል ውስጥ ስለፀሎት ለማስተማር የተጠቀመባቸው በህብረተሰብ መሃል የሚገኙ ሁለት አይነት ግንኙነቶች ምንና ምንድናቸው? ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተናገራቸው ሁለት ምሳሌዎች ተጠቅሞ ለደቀ መዛሙርቱ ሊያስተላልፍ የፈለጋቸውን ቢያንስ ሁለት ሃሳቦች ተናገር።
3. ቁ14-23 ባለው ክፍል ውስጥ ስናነብ፤ ኢየሱስ ድዳውን ጋኔን በማውጣቱ ምክንያት በዚያ የነበሩት ሰዎች ስለሁኔታ ቢያንስ ሶስት ዓይነት የተለያየ አመለካከትና ሃሳብ እንደሰጡ ይታያል፤ እነዚህ ሶስት ዓይነት አስተሳሰቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በቁ17 ጀምሮ ኢየሱስ ከነዚህ ሶስት ዓይነት ሰዎች መሃል ለአንደኛቸው መልስ የሚሆነውን ነገር ሊያስረዳቸው ሲሞክር እንመለከታለን፤ መልሱ ያነጣጠረው በየትኞቹ ዓይነት ሰዎች ላይ ነበረ?
4. በቁ21 እና 22 ውስጥ ኢየሱስ የተናገረው ምሳሌ ከቁ14 ጀምሮ ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ በምን መንገድ እንደሚያያዝ አስረዳ። እንደገና ደግሞ ኢየሱስ በቁ24-26 ላይ ከዚሁ ከርኩስ መንፈስ ጋራ የተያያዘውን ሃሳብ መናገር ሲቀጥል እናገኘዋለን፤ በዚህኛው ክፍል ውስጥ የተናገረው ሃሳብ በተለይ በማን ላይ ያነጣጠረ ነው ብለህ ታምናለህ?
5. በቁ29-32 ላይ ስናነብ ጌታ ኢየሱስ ያ ትውልድ ምልክትንና ተአምራትን የመፈለጉን ነገር በምን መልኩ ነው ሲመለከተው የምናየው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ምልክትንና ተአምራትን ለሚጠይቁት ሰዎች ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደሆናቸውና ስብከቱን እንደተቀበሉ በመናገር፤ የሰው ልጅም እንዲሁ ምልክት ይሆናቸዋል ሲል፤ አንደኛ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት የሆነው በምን መንገድ ነበረ? ደግሞስ ኢየሱስ ራሱን ከዮናስ ምልክትነት ጋራ ማስተያየት የፈለገው የትኛውን ሁኔታ ነው?
6. ቁ33-36 ላይ ጤናማ የሆነ ሰው መብራትን አብርቶ ከእንቅብ በታች እንደማያስቀምጥና፤ ዓይናችን ደግሞ ብርሃን እስከሆነና እስካልጨለመ ድረስ ሰውነት ሁሉ እንደሚጠቀም ተናግሮ፤ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት በቁ35 ላይ ኢየሱስ ከሰጠው ማስጠንቀቂያን ምን ሊለን እንደፈለገ ተናገር። ቁ37-41 ላይ ኢየሱስና ፈሪሳዊው ባደረጉት ውይይት ውስጥ ስንመለከት፤ ለዚህ ፈሪሳዊ ኢየሱስ ሊያስተምረው የፈለገው አንድ አጭር እውነት ምን ነበረ?
7. በቁ42-54 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ጌታ መልዕክቱ በወዮላችሁ የተሞላ ነው። በተለይ ቁ42 ላይ ኢየሱስ ፈሪሳውያኑ የሚወቅስበት ጉዳይ ምን ነበረ? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ፈሪሳውያኑን የነቀፈባቸውን ሃሳቦች በሙሉ በአንድ ቃል ግለጽ ብትባል ምን ትላለህ?
8. ጌታ ኢየሱስ በነዚህ 42-54 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ለጻህፍትና ለፈሪሳውያን ያስተላለፋቸው መልዕክቶች ምን ያህሉ እውነት ነበሩ ብለህ ታምናለህ? ታዲያ እውነት ከሆኑ ለምን በቁ53-54 ያለው ነገር ደረሰበት? ለሰዎች እውነቱን መናገርህ ከተቀባይነት ይልቅ አንዳንዴ ጥላቻንና መገለልን ሊያመጣብህ እንደሚችል መረዳት ይጠቅማል።

# ጥናት አሥራ ሰባት ሉቃስ 12፡1-59

የጥናት ዓላማ፡- እኛ ያለንበትን ዘመን ብንመረምርና ብዙም ሳንሄድ በአካባቢያችን የምንሰማውን፣ የምናነበውንና የምናየውን ዜና ብቻ ብናስተውለው፤ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጫ በደጅ እንደሆነ፤ ስለዚህም የተጣለብንን አደራ ለመወጣት ጊዜው አጭር መሆኑን አውቀን በትጋት ሥራችንን ለመሥራት የሚያነቃቃን እውነት መሆኑን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እናንት ግብዞች፤ የሰማዩንና የምድሩን መልክ መመርመር ታውቃላች፤ ታዲያ ይህንን የአሁኑን ዘመን መመርመር እንዴት ተሳናችሁ?" ሉቃ 12፡56

1. ሉቃስ 12፡1-59 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ኢየሱስ ለተሰበሰበው ህዝብ የተናገረው አንድ ማስጠንቀቂያ ምን የሚል ነበረ? በቁ2-3 ላይ የተነገረው ሃሳብ በምን መንገድ ነው በቁ1 ላይ ከሰፈረው ሃሳብ ጋራ የሚገናኘው? በቁ4-7 አነጋገር ሰዎችን እንዳንፈራ ነገር ግን እግዚአብሄርን እንድንፈራ ይመክረናል፤ ሰውን አለመፍራትና እግዚአብሄርን ግን ስለመፍራት ምክንያት አድርጎ የሰነዘራቸው ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. ቁ8-12 ላይ በተለይም ቁ11 ላይ "ሰዎች ይዘው ወደ ምኩራብ፣ ወደ ገዥዎችና፣ ባለሥልጣናት ባቀረቧችሁ ጊዜ…" እያለ ይናገራል፤ እነዚህ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ስለሚችሉበት ምክንያት ከነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ማየት የምትችለው ነገር ካለ ተናገር። ቁ13-15 ላይ ውርስን ከወንድሙ ጋራ ኢየሱስ እንዲያከፋፍላቸው ለጠየቀው ሰው መልስ ከሰጠ በኋላ፤ እዚያ ተሰብስቦ ይሰማው ለነበረው ህዝብ የተናገረውን ስታነብ የትምህርቱ ዋነኛ ሃሳብ ምን ነበረ ብለህ ታምናለህ?
3. በቁ16-21 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ምሳሌ ላይ የምናየው ሰው በተለይም በቁ18 እና 19 ላይ ስንመለከተው እግዚአብሄር በምንም መንገድ ለወደፊት በሚነድፈው እቅዱ ውስጥ እንደሌለ የሚጠቁሙንን ቃላት ለይተህ ተናገር። በአንተ አመለካከት ይህንን ሰው "አንተ ሞኝ" ሊያሰኘው የቻለው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? በቁ21 ላይ ኢየሱስ ለተናገረው ምሳሌ አጠቃላይ ሃሳብና እንዲማሩ የፈለገውን ነገር ምን ነበረ?
4. ቁ22-34 ላይ ስንመለከት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱን ከሁለት ነገሮች ጋራ እያወዳደረ አንድ ትልቅ እውነትን ሊያስተምራቸው ሲሞክር እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ቁ23 ላይ ደግሞ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ስለሚበሉትና ስለሚለብሱት እንዳይጨነቁ ሲያስተምራቸው "ህይወት ከምግብ፣ ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና።" በማለት የተናገረው ምን ለማለት ፈልጎ ነው ብለህ ታምናለህ?
5. ከቁ27-34 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሄርን ለእኛ ምን እንደሆነልን አድርጎ ነው የሚናገረው? እነዚህን ቁጥሮች በምናነብበት ጊዜ፤ እኛ የእግዚአብሄር ልጆች የተባልነው አማኞች በአለም ካሉት ከሌሎች ሰዎች የተለየን ሆነን መገኘት እንደሚኖርብን የሚጠቁመን ክፍል የትኛው ነው? ክፍሉ የሚያስተምረን ከእነርሱ ልዩ ሆነን መገኘት የሚኖርብን ዋነኛው ነገር ምንድነው?
6. በቁ37-34 ባየናቸው ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄርን እንደ አባታችን አድርጎ ሲስልልን ተመልክተናል፤ በ38-45 በሰፈረው ምሳሌ ደግም ስንመለከት እግዚአብሄርን በምን አይነት ነው ከእኛ ጋራ ያለውን ግንኙነት ሊገልጽ የሚሞክረው? በቁ47-48 ላይ የምንመለከታቸው ሁለቱ አይነት አገልጋዮች ማንና ማን ብለን ልንጠራቸው እንችላለን? ላደረጉት ነገር የሚደርስባቸውን ቅጣት አስመልክቶ፤ በእነዚህ ሁለት ዓይነት አገልጋዮች ሊሆን ያለውን ከዚህ ክፍል ምን ትረዳለህ? የአንተስ የምታጠፋው ፈቃዱን እያወቅህ ነው ወይስ ፈቃዱ ምን እንደሆነ ባለማወቅ?
7. በቁጥር 51 ላይ "በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ ይመስላችኋል?…እኔ የመጣሁት ለመለያየት ነው።" በማለት ኢየሱስ ሲናገር፤ በዮሐ 14፡27 ላይ ደግሞ "…ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም" በማለት ይናገራል። በእነዚህ ሁለት ሃሳቦች መሃል ያለ የሚመስለውን ቅራኔ አብራራ።
8. በቁ54-56 ላይ ኢየሱስ አድማጮቹን ምን እንዲያደርጉ ነው የሚያበረታታቸው? እነዚህ ሰዎች የነበሩበትን ዘመን እንዲመረምሩ ያበረታታው ኢየሱስ ለእኛስ ምን የሚለን ይመስልሃል? አንተስ ያለህበትን ዘመን ትመረምራለህ ወይ? ለጌታችን ዳግም ምጻት እንድንዘጋጅ የሚጠቁሙን በአካባቢያችን የሚካሄዱ ምልክቶችን ለመለየትና ለማወቅ የተከፈቱ ዓይኖች ሊኖሩን ያስፈልጋል።

# <u>ጥናት አሥራ ስምንት ሉቃስ 13፡1-35</u>

የጥናት ዓላማ፡- የሄሮድስ ማስፈራራት ኢየሱስን ከተልዕኮው እንዳላንቀሳቀሰው ሁሉ፤ እኛም ከእግዚአብሄር የተቀበልነውን ተልዕኮ ለማጨናገፍ ለሚነሳ ወሬም ሆነ ማናቸውንም ማስፈራሪያ ሰምተን በፍርሃት ሥፍራችንን መልቀቅ እንደማይኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…ሄሮድስ ሊገልህ ስለሚፈልግ ተነስተህ ከዚህ ሂድ አሉት። እርሱም እንዲህ አላቸው፤ ሄዳችሁ ለዚያ ቀበሮ፤ እነሆ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ፤ ህመምተኞችን እፈውሳለሁ፤ በሶስተኛውም ቀን ከግቤ እደርሳለሁ ብሏል በሉት።"

1. ሉቃስ 13፡1-35 በአንድነት ይነበብ። 1-5 ላይ ስናነብ፤ ጲላጦስ ያደረገውን አስከፊ ነገር ከነገሩት ሌላ ኢየሱስ ራሱ ተጨማሪ የነበረው ዜና ወይም መረጃ ምን ትመለከታለህ? ሰበር ዜናውን ይዘው ወደ ኢየሱስ የሚያመጡ ሰዎች እንደነበሩ እናነባለን። እነዚህ ሰዎች ይዘውለት የሚመጡትን ዜና ወይም ወሬ ሲጠቀምበት የምንመለከተው በምን ዓይነት መንገድ ነው? ከዚህ ሁኔታ ለራሳችን ህይወት የሚሆን ምን ትምህርት ማግኘት እንችላለን?
2. በቁ1-5 እና በቁ 6-9 ውስጥ ባሉት ሃሳቦች የጋራ የሆነ አንድ የምንመለተተው ሃሳብ ምንድነው? የእርሻው ባለቤት በበለሲቱ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ የወሰነባቸው ዋና ምክንያቶች ምን ምንድናቸው? የአትክልት ሰራተኛው ለመሬቱ ባለቤት የለሷን ዕጣ ክፍል አስመልክቶ ለእርሻው ባለቤት ሲያማክር የምንመለከተው ሃሳብ ምንድነው?
3. ቁ10-13ትን ስንመለከት ኢየሱስ እያደረገ የነበረው ነገር ምንድነው? ይህች ሴት አይሁዳዊ ስለሆነች ምናልባትም አስራ ስምንቱንም ዓመታት ፈውሷን ሳታገኝ እንደኀበጠች ወደ ምኩራብ ስትመላለስ እንደነበረ እንገምታለን፤ ለሴትየዋም ሆነ በምኩራቡ ለተሰበሰቡት ሰዎች በአንተ አመለካከት የዛሬውን ቀን የተለየ የሚያደርገው ነገር ምንድነው ትላለህ? ከዚህ ሁኔታ መማር የምንችለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
4. ቁ15-16 ላይ የምኩራቡን አለቃ ያስቆጣውና ህዝቡን እንዲገስጽ ያደረሰው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስ ይህች ሴት አንዲት ተጨማሪ ቀን በዚህ ሁኔታ ማሳለፍ እንደማይኖርባት ኢየሱስ አረጋግጦ ተናግሯል፤ ለዚህ አመለካከቱ ምክንያቶች አድርጎ የሰጣቸው በዚህ ክፍል የምታያቸውን ነገሮች ዘርዝር። ኢየሱስ የምኩራቡ አለቃ ሰንበትን አስመልክቶ ላመጣው የተቃውሞ ሃሳብ የሰጠው መልስ በህዝቡ ዘንድ ያስከተለው ሁለት ዓይነት ስሜት ምን ነበረ?
5. ቁ18-21 በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄርን መንግሥት የመሰለባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? እነዚህን ሁለት ምሳሌዎች በመናገር ኢየሱስ የእግዚአብሄርን መንግሥት አስመልክቶ ሊያስተላልፍ የፈለጋቸው መልዕክቶች አሉ፤ እነዚህ መልዕክቶች ምን እንደሆኑ ተናገር።
6. ከ22-27 የምናየው ክፍል በተለይም ቁ26 እና 27 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን የማስጠንቀቂያ ሃሳብ ወደ ዛሬ እኛ ወደ ምንኖርበት ዘመን አምጥተን ስንመለከተው በምን ዓይነት መንገድ ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል ትላለህ? ሰዎች ራሳቸውን እንዳያታልሉና የእግዚአብሄርን መንግሥት ለመውረስ ማድርግ ይኖርባችኋል ብሎ የሚመክራቸው ነገር ምንድነው? መግቢያው በር ኢየሱስ ብቻ ሆኖ ሳለ ሰዎች የመንግሥተ ሰማያት መግቢያን በር በዘመናችን ሊያሰፉት የሚሞክሩብ በምን ዓይነት ነው?
7. በቁ28-30 ላይ ያለው ክፍል ስለ አብርሃም፣ ይስሃቅና ያዕቆብ በእርግጠኛነት እንድናውቀው የሚረዳን አንድ እውነት ምንድነው? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ "ሰዎች ከምሥራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ መጥተው በእግዚአብሄር መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ።" የሚለው አነጋገር፤ የእግዚአብሄርን መንግሥት ስለሚወርሱት ሰዎች ማንነት የሚጠቁመን ነገር ምንድነው።
8. በቁ31-35 ውስጥ በተለይም ደግሞ በቁ31 እና 32 ላይ ፈሪሳውያኑ ለኢየሱስ ያመጡለት ዜና ምን ዓይነት ስሜት ሊፈጥር የሚችል ዜና ነበረ? ይህ ዜና በኢየሱስ ስሜትና አገልግሎት ላይ ያስከተለው ምን ነገር ታያለህ? አንተስ እግዚአብሄር የሰጠህን ተልዕኮ ለማጨናገፍ የሚያስፈራራህ ሃይል አለ ወይ? ተልዕኮን ለማጨናገፍ ለሚነሳ ወሬም ሆነ ማናቸውም ማስፈራሪያ በመስማት ሥፍራህን እንዳትለቅ መጠንቀቅ ይኖርብሃል።

# ጥናት አሥራ ዘጠኝ ሉቃስ 14፡1-35

የጥናት ዓላማ፡- ሰዎች ኢየሱስን እንዲከተሉ ስንጠራቸው፤ ከእርሱ የምናገኛቸውን ድንቅ የሆኑ ነገሮች ሁሉ መናገር አስፈላጊ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፤ በአንጻሩ ግን ኢየሱስን መከተል የሚጠይቀው ዋጋም እንዳለ ጭምር መናገር ሰዎች የሚገቡበትን አውቀው እንዲገቡ ይረዳል።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "…የራሱንም ህይወት እንኳን ሳይቀር ባይጠላ፤ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም። የራሱንም መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።" ሉቃ 14፡26-27

1. ሉቃስ 14፡1-35 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ ስናነብ፤ ኢየሱስ ምግብ ሊበላ በፈሪሳዊው ቤት ሲገባ በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በአይነ ቁራኛ ይከታተሉት እንደነበረ ይነግረናል። እነዚህ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን በአይናቸው የሚከታተሉት ለምንድነው ትላለህ? ኢየሱስ በዚህ ክፍል ለፈሪስውያኑና ለህግ አዋቂዎቹ ያቀረበላቸው ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ምንም አይነት መልስ አለመመለሳቸው መልሱን ስለማያውቁት ነው ወይስ ለምን ይመስልሃል?
2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በወንጌሎች ውስጥ ሁሉ ኢየሱስ በሰንበት ስለመፈወሱ ከፈሪሳውያኑና ከአለቆች ሁሉ በየጊዜው ተቃውሞ እንደደረሰበት እናውቃለን። ለምንድነው ታዲያ ይህንን ያህል ተቃውሞ እየመጣበት ፈውሱን ወደሌላ ቀናት ማስተላለፍ ያልፈለገው? ቁ4-6 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚናገረው አነጋገርና በተለይም የሰጠውን ምሳሌ ስንመለከት፤ ከበሽታው የተፈወሰው ሰው ለኢየሱስ ምኑ እንደሆነ ነው የሚጠቁመን?
3. በቁ1 ላይ ሰዎቹ ኢየሱስ እያደረገ ያለውን ይከታተሉ እንደነበረ ስናይ፤ በቁ7 ላይ ደግሞ ማን የማንን ድርጊትን ሲከታተል ነው የምናየው? ኢየሱስን ይከታተሉት የነበሩት ሰዎች ስህተት ሊያገኙበት ችለዋል ወይ? ኢየሱስ በሰዎቹ ላይ ስህተት አግኝቷል የምትል ከሆነ ስህተታቸው ምን እንደነበረ ተናገር። እኛም ብንሆን በህይወታችን እንኳንስ እግዚአብሄር ሆነ ብሎ ፈልጎ ይቅርና በማናቸውም ሰዓት ውስጥ ርኩሰትን ሊያገኝብን ስለሚችል ንስሃ የየእለት ጸሎታችን ክፍል ሊሆን ይገባል።
4. በቁ7-11 ላይ ኢየሱስ በዚያ ለተገኙት ሰዎች የተናገረው ነገር ለመገሰጽ ነው ወይስ ለማስተማር ፈልጎ ነው ትላለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ። ጌታ ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለአድማጮቹ ሊያስተላልፍ ወይም ሊያስተምር የፈለገው አንድ ጭብጥ የሆነ እውነት ተናገር ብትባል ምን ትላለህ?
5. ኢየሱስ ስለተደረገለት ወይም ደግሞ ምግብ አብልቶኛል ብሎ እውነትን ከመናገር ዝም እንደማይል የምናውቀው እንዴት ነው? ለጋባዡ የሰጠው ምክር ከምን ተነስቶ ይመስልሃል? ለነዚህ ሁለት አይነት ሰዎች ማለትም፤ ለተጋባዥ እንግዶቹ በሰጠው ምክርና፣ ለጋባዡ ሰው በሰጠው ምክር መሃል የምታየው የሃሳብ ተመሳሳይነት ካለ ለወገኖች ለማስረዳት ሞክር።
6. ቁ15-24ትን ስናነብ ከኢየሱስ ጋራ ይመገብ ከነበሩት ሰዎች አንዱ "በእግዚአብሄር መንግሥት ቀርቦ ከማዕድ የሚበላ ብጹዕ ነው" በማለት ሲናገር ከኢየሱስ አንደበት የጠበቀው ምላሽ ምን ይመስልሃል? ኢየሱስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ይህ ሰው ለተናገረው ነገር በምሳሌ አድርጎ ያስቀመጠው ሃሳብ፤ በእግዚአብሄር መንግሥት ማዕድን ስለመብላት አስመልክቶ ለተናገረው ሰውዬ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በአጭሩ ምን ነበረ?
7. ቁ25-27 ላይ አንድ ሰው የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ለመሆን የግዴታ የሚያስፈልጉ ሆነው የተጠቀሱት ሁለት ዋነኛ ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በዚህ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ቤተሰቦችን በመዘርዘር ደቀመዝሙር ሊጠላ እንደሚገባው ይናገራል፤ ኢየሱስ ይህንን ሲል ጥላቻን እያስተማረ ነው ወይስ የተለየ ሃሳብ ለማስተላለፍ ፈልጎ ነው ትላለህ? ከሆነስ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ።
8. ቁ28-35 ላይ የህንጻንና የጦርነትን ምሳሌዎች በመናገር ለአድማጮቹ ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋነኛ ትምህርት ምንድነው ትላለህ? ከዚህ የሚገኘው ትምህርትስ በምን መንገድ ከቁ25-27 ከተናገረው ሃሳብ ጋራ ይዛመዳል? አንተስ ስለክርስቶስ ስትናገር ኢየሱስን መከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ ጭምር ትናገራለህ ወይ? የኢየሱስን ጥሪ ፈለግ እንከተል ካልን፤ ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለውንም ጭምር መናገር ግድ ነው።

# ጥናት ሃያ ሉቃስ 15፡1-32

የጥናት ዓላማ፡- የአንድ ነፍስ መዳን በእግዚአብሄር ልብ ውስጥና በሰማይ መላዕክት ዘንድ የሚፈጥረውን ታላቅ ደስታ ስንመለከት፤ እንዲያውማ ትናንት እኛ ከወጣንበት ጨለማ ውስጥ እግዚአብሄር ሰዎችን መንጥቆ ሲያወጣ ምን ያህል በደስታ መፈንደቅ እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “አባቱም እንዲህ አለው፡ ልጄ ሆይ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ ይህ ወንድምህ ግን ሞቶ ነበረ ህያው ሆነ፤ ጠፍቶ ነበረ ተገኘ፤ ስለዚህ ደስ ሊለንና ፍስሃ ልናደርግ ይገባናል።” ሉቃ 15፡31-32

1. ሉቃስ 15፡1-32 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ውስጥ የምናያቸውን ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን፤ በቁ25-30 ከምናየው ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ታላቅ ወንድም ጋራ የሚመሳሰሉበት አንድ ዋነኛ ነገር ምንድነው ትላለህ?
2. በቁ3-10 ላይ በምንመለከታቸው ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ የጠፉት አንዱ በግና አንዱ ሳንቲም በተገኙበት ወቅት የደስታ ተካፋይ ለመሆን የተጋበዙት ሰዎች እነማን ነበሩ?
3. ቁ11-16 ላይ የምናየው ታናሹ ልጅ በጊዜው የፈለገውና አባቱን የጠየቀው ነገር ምን ነበረ? ይህ ልጅ ምን አይነት አስተሳሰብ እንዳለውና ሊወስድ ያለው እርምጃ ሊጎዳው እንደሚችል ከአባትየው በላይ ሊያውቅ የሚችል እንደማይኖር ይታወቃል፤ ታዲያ ይህ ልጅ ወደፊት ሊጎዳው የሚችልና የማይጠቅመው ውሳኔ ውስጥ እንዳይገባ አባትየው ያልከለከለው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? ይህንን ወደ እኛና ወደ እግዚአብሄር ብናመጣው ልንማር የምንችለው እውነት ምንድነው?
4. ቁ17-20ን ስንመለከት ልጁ ልብ በገዛ ጊዜና ከራሱ ጋራ ተወያይቶ ወደ ቤቱ ለመመለስ በወሰነበት ወቅት እዚያ ደርሶ የሚናገራቸውን ነገሮች በአዕምሮው ሲያወጣና ሲያወርድ በመጨረሻ ሊናገር የወሰናቸው ሶስት ሃሳቦች ምን ምንድናቸው? ይህ ልጅ ቀድሞ ከእርሱ ጋራ ምንም ግንኙነት ሊኖረው እንደማይፈልግ በተግባሩ ገልጾ የተሰናበተውን ሰው በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ማን እያለ ነው የሚጠራው? በቁ20 ላይ የአባትየውን አቀባበል የፍቅር አቀባበል እንደሆነ የሚጠቁሙትን አምስት ሃሳቦች ተናገር።
5. ቁ21-25 ላይ “ልጁም አባቴ ሆይ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁ፤ ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም” በማለት ሲናገር “ከእንግዲህ” የሚለው አነጋገር የትኛውን ጊዜ የሚጠቁም ነው? ልጅየው ለአባቱ የተናገረውን ነገርና አባትየው መውሰድ የጀመረውን እርምጃ ስታነብ፤ አባትየው ልጁን አላደመጠውም ማለት ነው ወይስ በዚያን ወቅት የተካሄደው ነገር ምንድነው ትላለህ?
6. ቁ25-32 ላይ ታላቅ ወንድምየው በታናሽ ወንድሙ መምጣትና በቤታቸው ውስጥ እየተካሄደ ባለው ነገር የተሰማው ስሜት ምን ይመስል ነበረ? እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት፤ ታላቅ ወንድምየው ታናሹ ወንድሙ ባልነበረባቸው ጊዜያት በአባቱ ቤት ያሳለፋቸውን ዘመናት በተለይ ቁ29ኝን ስንመለከት ራሱን የተመለከተው እንደምን አድርጎ ነው? ከዚህ አንጻር የአባትየው አመለካከት ታላቅ ወንድሙ ስለራሱ ከነበረው አመለካከት የሚለየው እንዴት እንደሆነ ቁ31-32ትን በመመልከት ተናገር። አንተስ እግዚአብሄርን ማገልገልህን የምታየው እንደ መልካም እድል ይሆን ወይስ እንደ ባርነት?
7. ጠቅላላ ምዕራፍ 15ትን ስትመለከት በሶስቱም ምሳሌዎች ውስጥ የምናያቸውና በተደጋጋሚ የተነገሩ ሶስት ሃሳቦች ምን ምን እንደሆኑና፤ በተጨማሪ ደግሞ እያንዳንዳቸውን አንድ አንድ ቃላት ብቻ በመጠቀም ለመግለጽ ሞክር። ከእነዚህ ከሶስቱ መሃል ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶታል ብለህ የምታምነው የትኛው እንደሆነና የት የት ቦታ እንደተጠቀሰ በመዘርዘር ተናገር።
8. እነዚህ ምሳሌዎች ሁሉ በአንድ ነፍስ መዳን ምክንያት እግዚአብሄርና በሰማይ ያሉት መላዕክቱ ስለሚሰማቸው መዳን የሚያስተምሩን ሃሳብ ምንድነው? አንድ ነፍስ ሲድንና ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ሲቀላቀል በልብህ ውስጥ የሚፈጥረው የተለየ ስሜት አለ ወይ? እግዚአብሄርንና የሰማይ መላዕክትና ደስ የሚያሰኘው ነገር የእኛንም ልብ በደስታ ሊሞላው ይገባል።

# ጥናት ሃያ አንድ ሉቃስ 16፡1-31

የጥናት ዓላማ፡- የእምነት አባትና የእግዚአብሄር ጓደኛ በመባል የታወቀው አብርሃም እንኳን ሰውን ከሞተ በኋላ ከሲዖል ማውጣት እንደማይችል እንደተናገረ ሁሉ ፤ እኛም ማንኛውንም ሰው ከሲዖል መታደግ ከፈለግን ጊዜው አሁን እንጂ ከሞቱ በኋላ ማድረግ የምንችለው ነገር እንደማይኖር ከዚህ ታሪክ በመማር ዛሬውኑ ማድረግ የሚገባንን ማድረግ እንደሚኖርብን ልንገነዘብ ያስፈልገናል።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ከሁሉም በላይ ከዚህ ወደ እናንተ ማለፍ የሚፈልጉ እንደማይችሉ፤ እዚያ ያሉትም ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ትልቅ ገደል ተደርጓል።" ሉቃ 16፡26

1. ሉቃስ 16፡1-31 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ይህ ሃብታም ሰው በመጋቢው ወይም በባለ አደራው ላይ ደስ ያልተሰኘበትና ያገኘበት ጥፋት ምን ነበረ? ይበ1ኛ ቆሮ 4፡1-2 ላይ ከምታነበው፤ ከመጋቢ የሚጠበቁ ሌሎች ነገሮች እንዳሉ ቢታወቅም፤ አንደኛውና ዋነኛው ጳውሎስ የሚጠቅሰው ነገር ምንድነው? መጋቢው ከነበረበት ሥልጣን ሲሻር ሊሰራቸው እንደማይችል የተረዳቸው ሁለቱ የሥራ ዓይነቶች ምንና ምን ነበሩ?
2. ቁ4-8ትን ስንመለከት መጋቢው ሰው ከሥራው እንደሚባረር በተረዳበት ወቅት እርሻና ልመና እንደማያዋጡት ሲያው ያደረገው ነገር ምን ነበረ? ቁ8 ላይ ስናነብ "ጌታም አጭበርባሪውን መጋቢ በብልህነቱ አደነቀው" በማለት ጸሐፊው ይነግረናል። ጌታ በዚህ ክፍል ላይ የዚህን ሰው ብልህነት አደነቀ ሲል፤ አጭበርባሪነቱን ነው ወይስ ምኑን ይመስልሃል ያደነቀው?
3. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሃብታሙን ሰው መጋቢ አስመልክቶ ለደቀመዛሙርቱ ከተናገረው ምሳሌ በመነሳት በቁ9-13 ላይ ለሁላችንም ህይወት ትምህርት ሊሆኑ የሚችሉ ሶስት እውነቶች ሰፍረው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስት እውነቶች ምን ምን እንደሆኑ አጠር ባለ መልኩ ለወገኖች ተናገር።
4. በቁ14-15 ላይ የምንመለከታቸው ፈሪሳውያን በሌሎች ሥፍራዎች ውስጥ ከተመለከትናቸው ፈሪሳውያን የሚለዩበት አንድ ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስን ያስነቀፈው የትምህርቱ ትክክል አለመሆን ነው ወይስ ሌላ ምክንያት ታያለህ? ቁ15 ላይ "በሰዎች ዘንድ የከበረ በእግዚአብሄር ፊት የረከሰ ነውና" ሲል እነዚህን ፈሪሳውን ይህ አነጋገር የሚነካቸው በምን መንገድ ነው?
5. በቁ16-18 ላይ ከዮሐንስ በፊት በነበረው ዘመንና ከዮሐንስ በኋላ ባለው ዘመን መሃል ስላለው ልዩነት ኢየሱስ የሚናገረው እውነት ምንድነው? በቁ18 ላይ "ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፤ ከባሏ የተፋታችውንም ሴት የሚያገባ ያመነዝራል።" አሁን እኛ እየኖርን ባለንበት ዘመን ይህ ኢየሱስ የተናገረው አነጋገር በክርስቶስ ተከታዮች አካባቢ ምን ያህል ትኩረት የተሰጠው ነገር ነው ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ።
6. በቁ19-22 ላይ ባሉት ቁጥሮች ላይ ስናነብ ሁለቱን ሰዎች መግለጫ ሆነው የተነገሩትን ማናቸውንም ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ ሰዎች በአብዛኛው ነገራቸው የተለያዩ እንደሆኑ ስንመለከት፤ ለእነዚህ ሰዎች የጋራና ሁለቱንም እኩል እንዳደረጋቸው የምንረዳው አንድ ነገር ምን እንመለከታለን? ብዙ ባለንብረትና ባለጠጋ የሆነ ሰው፤ እንዲሁም ምንም የሌለውም ምስኪን ድሃ ሰው አንድ ቀን ሁለቱም ባዶ እጃቸውን ወደ መቃብር መውረዳቸውን ማስታወስ መልካም ነው።
7. ቁ23-26 ላይ ሞቶ በስቃይ ላይ የሚገኘው ሃብታም ሰው ለጠየቀው ጥያቄ የአብርሃም ሁለት መልሶች ምን እንደነበሩ በአጭሩ ለማስረዳት ሞክር። በዚህ ሥፍራ አብርሃም ለሃብታሙ ሰው እየነገረ ያለው አንተ በምድር ሃብታም ስለነበርክ ሲዖል የሚገባህ ሲሆን፤ አልዓዛር ደግሞ ድሃ ስለነበረ መንግሥተ ሰማያት ይገባዋል፤ ወይም ሰው ሃብታም ስለሆነ ሲዖል፣ ድሃ ስለሆነ ደግሞ መንግስተ ሰማያት ይገባል ማለቱ ነው ወይ?
8. ሃብታሙ ሰው የራሱን ነገር መቀየር እንደማይችል ተረድቶ ወንድሞቹ ወደ ሲዖል እንዳይመጡ ሲጠይቅ የአብርሃም መልስ ምን ነበረ? በሰውየው እምነት ወንድሞቹን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመጥራት የተሻለው መንገድ ምንድነው? አብርሃምስ ከዚህ አንጻር እምነቱ ምንድነው? አንተስ እንደአብርሃም ከተአምራት ይልቅ ሰዎችን ለማዳን ለእግዚአብሄር ቃል ሥፍራ ትሰጣለህ ወይ?
9. ቁ26 ላይ አብርሃም ለሃብታሙ ሰው ማንም ማድረግ የማይችለው ነገር እንደሆነ ማሳየት የፈለገው ነገር ምንድነው? ሰዎችን ከሲዖል አሻግረን ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ማስገባት የምንችልበት እድል ሰዎች በህይወት እስካሉ ብቻ እንጂ አንዴ ከሞቱ በኋላ ምንም ማድረግ እንደማንችል አውቀን አሁኑኑ የወንጌልን ሥራ መሥራት ያስፈልገናል።

# ጥናት ሃያ ሁለት ሉቃስ 17፡1-37

የጥናት ዓላማ፡- በአለም ያሉ ሰዎች እንደኖህና እንደሎጥ ዘመን ሁሉ ነገር እንደነበረ እንደሚኖር በማሰብ በየእለት ተግባራቸው እንደሚዋጡ፤ እኛ ግን የጌታችን መምጫ በማናቸውም ጊዜ ሊሆን እንደሚችል በማወቅ ታጥቀንና ተዘጋጅተን መጠበቅ እንደሚኖርብን ለመማር፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “በኖህ ዘመን እንደሆነው ሁሉ በሰው ልጅ ዘመንም እንዲሁ ይሆናል። ኖህ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ይበሉና ይጠጡ፤ ያገቡና ይጋቡ ነበር፤ የጥፋትም ውሃ መጥቶ ሁሉን አጠፋቸው።” ሉቃ 17፡26-27

1. ሉቃስ 17፡1-37 በአንድነት ይነበብ። በቁ3 እና 4 ላይ ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን ነገር፤ ከማቴ 18፡15 ትና ከምሳሌ 27፡5 ጋራ በአንድነት ስንመለከትታቸው ይህ ወንድምን መገሰጽ የሚለው ሃሳብ አላውማና ግቡ ከምን ጋራ የተያያዘ ነው ብለህ ታምናለህ? ቁ3-4ትን በምታነብበት ጊዜ ለብዎቻችን ምናልባትም አንተንም ጨምሮ አስቸጋሪ ብለህ የምታየው የትኛው ሃሳብ እንደሆነ ሃሳብህን በመስጠት ከወገኖች ጋራ ጊዜ ሰጥታችሁ ተወያዩበት።
2. በቁ5-6 ላይ እምነት እንዳላቸው አድርገው ያሰቡት ሐዋርያት መምህራቸውን የጠየቁት ጥያቄ ምን ነበረ? ጌታ ለሐዋርያቱ በቁ 6 ላይ የመለሰላቸውን መልስ ስትመለከት፤ በእርሱ አመለካከት እነዚህ ለብዙ ጊዜ የተከተሉትና ከደቀ መዝሙርነትነት አልፈው የቅርብ ሐዋርያቱ እንዲሆኑ የመረጣቸው ሰዎች እምነትን አስመልክቶ ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ግልጽ ሆኖ ባይጻፍም እንኳን ኢየሱስ እምነት እንደሚያስፈልጋቸው እንጂ እንደሚሰጣቸው ወይም ከየት እንደሚያገኙት በዚህ ክፍል ውስጥ አልነገራቸውም። አንተስ እምነትን ለማግኘት የምትፈልገውና የምትሄደው ወዴት ነው?
3. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቁ7-10 ባለው ክፍል ውስጥ የተናገረው ምሳሌ ላይ ላዩን ብቻ ሲታይ ጌቶች አገልጋዮቻቸውን በጭቆና መግዛታቸውን የሚያበረታታ ሆኖ ሊታይ ይችላል፤ ለምንድነው ቆላ 4፡1ን ስናነብ ይህ አይነቱ አመለካከት የተሳሳተ መሆኑን የምንረዳው? ቁ9 እና 10ርን ስንመለከት፤ ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ የተናገረበትን ምክንያት ግልጽ አድርጎ አስፍሮታል፤ የምሳሌው ዋነኛና ማዕከላዊ መልዕክት ምንድነው ይላል ኢየሱስ? አንተስ ለአገልግሎትህና ለልፋትህ ክፍያ የሚሆን ከሰውም ሆነ ከእግዚአብሄር የምትጠብቀው ምስጋና ይኖር ይሆን?
4. በቁ13 እና 14 ላይ የምናያቸው ለምጻሞች ኢየሱስ ኢንዲፈውሳቸው በሚለምኑበት ወቅት የለመኑበትን ሁኔታና፤ በቁ 15-16 ላይ ከለምጹ የነጻው ሳምራዊ ተመልሶ ኢየሱስን ያመሰገነበትን ሁኔታ በማነጻጸር ተናገር። በቁ19 ላይ “ተነስተህ ሂድ…” የሚለው የኢየሱስ አነጋገር ሰውየው በጊዜው ስለነገረበት ሁኔታ የሚጠቁመን ነገር ምንድነው?
5. በቁ20 እና 21 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥተ ሰማያትን አስመልክቶ አድማጮቹ ወይም ጠያቂዎቹ እንዲያውቁት የፈለጋቸው ሶስቱ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
6. ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በቁ22-25 በተለይም በቁ24 ላይ መምጣቱን አስመልክቶ ሲናገር “…መብረቅ በርቆ ሰማዩን ከዳር እስከዳር እንደሚያበራ፤ የሰው ልጅም በሚመጣበት ቀን ልክ እንደዚሁ ይሆናል” ይላል። ኢየሱስ ይህንን ሲል በአጭሩ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
7. በቁ26-37 ያሉት ቁጥሮች በአንድነት ይነበቡ። ቁ30 ላይ “የሰው ልጅ በሚገለጥበትም ቀን እንደዚሁ ይሆናል።” በማለት የጌታን መምጣትና የመገለጡን ቀን ኢየሱስ ከሁለት ከታወቁ ዘመኖች ጋራ በማነጻጸር ይናገራል፤ እነዚህ ሁለት ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። በነዚህ በተጠቀሱት ሁለት ዘመኖች ውስጥ ይካሄዱ የነበሩት ነገሮች ምን ምን ዓይነት ነገሮች ነበሩ?
8. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በቁ26-37 የተናገረውን ሃሳብ በሁለት ወይም በሶስት ቃላት ተናገር ብትባል ምን ትላለህ? አንተስ ለኢየሱስ መምጣት ተዘጋጅተሃል ወይስ እንደሌሎች ሰዎች ሁሉ ነገር እንደቀድሞው እያስኬድከው ነው? ኢየሱስ ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ሰዓት ስለሚመጣ ለሌሎች ድንገተኛ እንደሚሆንባቸው ለእኛም ድንገተኛ እንዳይሆንብን ተዘጋጅተንና መቅረዛችን በርቶ ልንጠብቀው ያስፈልገናል።

# ጥናት ሃያ ሶስት ሉቃስ 18፡1-42

የጥናት ዓላማ፡- ይህ እውር የአይኑን ብርሃን ተቀብሎ ወደ ልመናው እንዳልተመለሰ ሁሉ፤ እኛም ከጌታ በነጻ የምንቀበላቸው ማንኛቸውም በረከቶች ሁሉ በምስጋና ተሞልተን ከእርሱ ጋራ እንድንጣበቅና እርሱን አብዝተን እለት እለት እንድንከተለው የሚረዱን ሊሆኑ ይገባል።

የምናሰላስለው ጥቅስ:- "ሰውየውም ወዲያውኑ ማየት ቻለ፤ እግዚአብሄርንም እያከበረ ኢየሱስን ተከተለው" ሉቃ 18፡43

1. ሉቃስ 18፡1-42 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-5 ውስጥ አንደኛው ፍርድን የሚለምን፤ ሌላኛው ደግሞ ፍርድን መስጠት የሚችል ነገር ግን ፍርድ ለመስጠት የማይፈልጉ ሁለት ዓይነት ሰዎችን ያሳየናል። ፍርድ ለመስጠት ፈቃደኛ ስላልሆነው ሰው ምንባቡ የሚነግረንን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር። ስለዚህ ሰው በግልጽ የተነገሩን ባህርያቱ፤ በተለይም ይህችን ፍርድ የምትለምነው ሴት የምትገኝበት ሁኔታና ማንነቷ የበለጠ ተጠቂ ሊያደርጋት የሚችለው እንዴት እንደሆነ አስረዳ።
2. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ክፍል ውስጥ የዳኛውንና የመበለቲቱን ምሳሌ በቁ1-8 ውስጥ ሲነግረን፤ ትምህርቱ በአብዛናው ያተኮረው በዳኛው ላይ ወይስ በመበለቲቱ ላይ ይመስልሃል? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ። ብዙዎች ይህንን ምሳሌ ጨርሰው እንኳን ሳያነቡ እግዚአብሄርን ከዳኛው ባህርይ ጋራ ማነጻጸር ይጀምራሉ። ይህ ዳኛ እግዚአብሄርን የማይወክልባቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮችን በመዘርዘር ተናገር።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ በቁ9-14 ላይ የሰፈረውን ምሳሌ ከተናገረ በኋላ ምሳሌውን ያጠቃለለበት ሃሳብ ምን የሚል ነበረ? ይህ ኢየሱስ የተናገረውን ምሳሌ ያጠቃለለበት ሃሳብ ትዕቢተኞችንና በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸውን የሚያዋርዱትን ሰዎች የሚነካ ከሆነ፤ እነዚህን ከላይ ከተመለከትናቸው ሁለት ሰዎች ጋራ በምን ዓይነት መንገድ እንደሚገናኝ አስረዳ።
4. በቁ1-8 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን ምሳሌና በቁ9-14 የተነገረውን ምሳሌ የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር ምንድነው? እነዚህን ሁለት ምሳሌዎችስ አንደኛውን ከሌላኛው የሚለያቸውስ ነገር ምንድነው ትላለህ? በተለይ ቁ9 ላይ የተነገረውን ሃሳብ ስንመለከት እግዚአብሄር የሚጸየፋቸውና በእርሱ ፊት ሰውን ትዕቢተኛ እንደሆነ የሚያስቆጥሩትን ሁለት ዓይነት ነገሮች ሰፍረው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
5. በቁ15-17 ላይ ስናነብ ህጻናትን ወደ ኢየሱስ ማምጣትን አስመልክቶ በኢየሱስና በደቀ መዛሙርቱ መሃል ያለው የአስተሳሰብ ልዩነት ምን እንደሚመስል በራስህ ቋንቋ አስረዳ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ በተለይም በቁ17 ላይ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሄርን መንግሥት እንደ ህጻን የማይቀበል ሁሉ ከቶ አይገባባትም።" ብሎ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
6. ይህ በቁ18-30 ላይ የምናየው ሰው፤ በእውነት የእግዚአብሄርን ህግ መጠበቁንና በሙሉ ልቡ ደግሞ ጌታ አምላኩን መውደዱን የሚወድ እንደሆነ በተግባር ማረጋገጥ እንዲችል የተጠየቀው አንድ ጥያቄ ምን ነበረ? ለዚህ ሰው ኢየሱስን ለመከተል እንቅፋት ሆኖበት የምናየው ነገር ምንድነው? ለምንድነው ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሊመጡና ሊከተሉት ፈቃደኛነት ለሚያሳዩት ሰዎች እንዲከተሉት ነገሮችን ከማቅለል ይልቅ የሚያከብድባቸው የሚመስለው?
7. በቁ31-34 ላይ ስናነብ ሰዎች በኢየሱስ ላይ የሚያደርጓቸውና ኢየሱስ ደግሞ ራሱ የሚያደርገው ነገር በዝርዝር ሰፍሯል። እነዚህ ሰዎች በእርሱ ላይ ሊያደርጉ ያላቸውና ኢየሱስ ደግሞ ሊያደርግ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
8. በቁ18-23 ላይ የምናየው ሰው እስከዛሬ ሲለምን የቆየው ምን ለማግኘት ነበረ? በተለይም ቁ42 እና 43ትን ስናነብ፤ ይህ ሰው ከኢየሱስ ፈውስን በመቀበሉ ምክንያት የህይወቱን አቅጣጫ በምን መንገድ ተቀይሯል ትላለህ? አንተስ ከኢየሱስ የምትቀበለው በረከት በመንፈሳዊ ህይወትህ ለውጥ ያስከትላል ወይ? ከኢየሱስ ክርስቶስ በነጻ የምንቀበላቸው ማናቸውም በረከቶች በምስጋና ተሞልተን ከእርሱ ጋራ እንድንጣበቅና እርሱን አብዝተን እለት እለት እንድንከተለው የሚረዱን ሊሆኑ ይገባል።

# ጥናት ሃያ አራት ሉቃስ 19፡1-48

የጥናት ዓላማ፡- የምትታየዋ የክርስቶስ ቤተክርስትያን ዛሬ ለእኛ ተስፋ በሚያስቆርጥ አይነት ወንበዴዎችን ያዘለች ሆና ብናይም እንኳን፤ አንድ ቀን ግን እግዚአብሄር በራሱ ቀን ተገልጦ ጅራፍ ለሚገባው ጅራፍን፤ ለትምህርት ራሱን ላዘጋጀውም ትምህርትን እንደሚሰጥ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሻጮችን ከዚያ አስወጣ፤ ደግሞም ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል፤ ተብሎ ተጽፏል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው። በየቀኑም በቤተ መቅደስ ያስተምር ነበር” ሉቃ 19፡45-47

1. ሉቃስ 19፡1-48 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ዘኪዎስ ስለሚባለው ሰው ማንነት የምታያቸውን ማናቸውንም ነገሮች ዘርዝር። በቁ4 ላይ “ኢየሱስ በዚያ መንገድ ያልፍ ስለነበረም ወደፊት ሮጦ አንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ።” በማለት ይነግረናል። የዚህን ሰው ማንነቱን አስመልክቶ፤ ኢየሱስን ለማየት የወሰደውን እርምጃ እንዳይወስድ ሊያግዱት የሚችሉ ምን ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ ትላለህ?
2. በሉቃ 18፡22-23 ላይ ያለውን ሃብታም ሰውና በሉቃ 19፡5-8 ላይ ያለውን ሃብታሙን ዘኬዎስ ሁኔታ ስናነጻጽር፤ በተለይም ንብረትን አጥቶ ኢየሱስን ማግኘት ከሚለው ሃሳብ አንጻር ሁለቱን ሰዎች በማነጻጸር ተናገር። ቁ9 ላይ ኢየሱስ ስለዘኬዎስ “ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለሆነ፣ ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቷል።” ሲል፤ ዘኪዎስን በዚህ ሥፍራ የአብርሃም ልጅ እንዲባል ያበቃው ነገር ምንድነው?
3. ቁ11-13 ላይ ስናነብ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከምንመለከተው መስፍን የሚነግዱበትን ገንዘብ የተቀበሉት ሰዎች ቁጥር ምን ያህል ነበረ? ከቁ15 ጀምሮ ያሉትን ቁጥሮች ስንመለከት ይህ ሰው የሰጣቸውን ገንዘብ አትርፈውበት እንደሆነና እንዳልሆነ የጠየቃቸው ሰዎች ቁጥርስ ምን ያህል ነበረ? ታሪኩን ከቁ ከቁ11-27 በአጠቃላይ ስናነብ የተጠየቁት ሰዎች ቁጥር ገንዘብ ከተቀበሉት ቁጥር በጣም ያነሰ ነው፤ ሌሎቹ የተቀበሉት አልተጠየቁም ለማለት ነው ወይስ ለምን በሶስት ብቻ ያበቃ ይመስልሃል?
4. በዚህ ታሪክ ውስጥ መስፍን በመባልና የንጉስነት ማዕረግ ለመቀበል የሄደ፣ ንጉስ ሆኖ የሚመጣና፣ የሰጠውን አትርፎ የሚቀበል የተባለለት ማን ይመስልሃል? ለምን ይህን ማለት እንድቻልክ አስረዳ። ቁ20 እና 21ድን ስንመለከት ሶስተኛው አገልጋይ የተሰጠውን ገንዘብ እንዳይነግድና እንዳያተርፍ የያዘው ነገር ምን እንደሆን ለጌታው ሲነግር እናነባለን፤ ይህንን ሰው ሰርቶ እንዳያተርፍ የከለከለው ነገር ምን እንደነበረ በአንድ ቃል ተናገር። አንተስ በተሰጠህ ስጦታ እንዳትሰራበትና ፍሬ እንዳታፈራ ፍርሃት የሆነበህ ነገር ምን ይሆን?
5. ቁ24-27 ላይ ያለው ክፍል በአንድነት አንብቡት። ቁ24 ላይ “ምናኑን ውሰዱበትና ዐሥር ምናን ላለው ስጡት አላቸው።” ይላል ይህ አነጋገሩ እዚያ በነበሩት ሰዎች አመለካከት ትክክለኛ ፍርድ ሆኖ አልታያቸውም፤ የእነርሱ ተቃውሞ ምን የሚል ነበረ? ንጉሱ እነርሱ ላመጡት ተቃውሞ የመለሰው ምላሽ “እላችኋለሁ ላለው ሁሉ ይጨመርለታል፤ የሌለው ግን ያው ያለው እንኳን ይወሰድበታል።” የሚል ነበረ። ንጉሱ ይህንን ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. ቁ32 ላይ “የተላኩትም ሄደው ልክ እንደነገራቸው ሆኖ አገኙት” ይላል። እነዚህ መልዕክተኞች የተነገራቸው ነገር ምን ነበረ? ቁ32-35ትን ስናነብ የተላኩት ሰዎች ልክ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው ሲያደርጉ እናያለን። ይህ ሁኔታ በተካሄደበት ወቅት አንተ ከተላኩት ሁለት ሰዎች መሃል አንዱ ብትሆን፤ ከዚህ ሁኔታ ሁሉ የሚያስደንቁህ ነገሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ተናገር።
7. በቁ37-44 ላይ በምናነበው ክፍል ውስጥ ለኢየሱስ እየተሰጠ ያለው አምልኮ እየቀለጠ የሄደው በምን ዓይነት ሥፍራ ነበረ? የኢየሱስ ማንነት ከኢየሩሳሌም እንደተሰወረባትም ክፍሉ ግልጽ አድርጎ ይነግረናል፤ በዚህ ክፍል ኢየሩሳሌምን ይወክላሉ ሊባሉ የሚችሉ እነማንን ታያለህ?
8. ቁ45-48 ውስጥ ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ሁለት ነገሮችን ሲያደርግ እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች በቅደም ተከተል ምንና ምንድናቸው? አንተስ በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ኢየሱስ ከወንበዴ ከሚቆጥራቸው ውስጥ ነህ ወይስ ከእርሱ ለመማር ከተዘጋጁት? የእግዚአብሄር ቤት የጸሎት ቤት መሆኑ ተረስቶ ብዙ የተለያዩ ነገሮች የሚካሄድበት ሥፍራ ሆኗል፤ ሆኖም ኢየሱስ ቤቱን የሚያጠራበት ቀን ስላለ ወንበዴዎች ሳንሆን ተማሪዎቹ ሆነን እንድንገኝለት ይርዳን።

# ጥናት ሃያ አምስት ሉቃስ 20፡1-47

የጥናት ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ቃል የተሰጠን ዋነኛ ምክንያት እንድንታዘዘውና በመታዘዛችንም ደግሞ ህይወት እንዲሆንልን እንጂ፤ ከሰዎች ጋራ በሚኖረን ቅራኔና የሃሳብ አለመግባባት ድል ለማድረጊያ የሚረዳን የጦር መሳሪያ አድርገን እንድንጠቀምበት እንዳልሆነ ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ትንሳኤ ሙታን የየለም ከሚሉት ሰዱቃውያን አንዳንዶቹ ወደ ኢየሱስ መጥተው ጥያቄ አቀረቡለት፤ እንዲህም አሉት፤ መምህር ሆይ፤ አንድ ሰው ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣ ወንድሙ መበለቲቱን አግብቶ ልጆች በመውለድ ለወንድሙ ዘር እንዲተካ ሙሴ ጽፎልናል።" ሉቃ 20፡27-28

1. ሉቃስ 20፡1-47 በአንድነት ይነበብ። በ19፡47-48 ላይ ኢየሱስን ለመግደል ይፈልጉ የነበሩት ሰዎች በ20፡1-2 ላይ ይህንን ሃሳባቸውን ለማስፈጸሚያ የሚረዳቸው አድርገው ያሰቡትን ጥያቄዎች ሲያቀርቡለት እናያለን። እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? ኢየሱስንስ በቁ1-2 ላይ ስናነብብ የጠየቁት ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ነበሩ?
2. እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ጥያቄአቸውን በጥያቄ በመመለስ ባፋጠጣቸው ወቅት መልሱን ለመስጠት ያደረጉትን ውይይት መሰረት በማድረግ፤ ከእነርሱ አመለካከት እንደምንረዳው አንድ ነገር አመጣጡ ከሰማይ ከሆነ ምን ሊደረግ እንደሚያስፈልገው ነው የተስማሙት? በቁ4 ላይ "የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበር ወይስ ከሰው?" ይህ ከሰማይ የሚለውን አነጋገር ምን በሚል ቃል መተካት ይቻላል ትላለህ?
3. ከቁ9-19 ያለውን ምሳሌ በአንድነት አንብቡት። በነዚህ ቁጥሮች ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለህዝቡ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ የእርሻው ባለቤት መልዕክተኞችን በተደጋጋሚ ልኮ ገበሬዎቹ እንደደበደቧቸው፤ በመጨረሻም ልጁን ልኮ ደግም እርሱን እንደገደሉት ተናግሯል፤ እነዚህ ገበሬዎች የሚላቸው እነማን ናቸው? ቁ16 ላይ ኢየሱስ ምሳሌውን ሲያጠቃልል የእርሻው ባለቤት ስለሚያደርገው ነገር የሚናገረው ምንድነው?
4. ቁ16 ላይ "መጥቶ እነዚያን ገበሬዎች ያጠፋቸዋል፤ የወይኑንም ተክል ቦታ ለሌሎች ይሰጣል።" ብሎ ሲናገር፤ በዚህ ሥፍራ "ሌሎች" በመባል የተጠሩት እነማን ናቸው? ቁ19 ላይ ደግሞ ኢየሱስ ለህዝቡ የተናገረውን ምሳሌ ጸሐፍትና የካህናት አለቆች ሰምተው ምን ማለት እንደሆነም ስለገባቸው ወደ ንስሃ ከመምጣት ይልቅ ወደ ምንድነው የወሰዳቸው? አንተስ እግዚአብሄር በባሪያዎቹ ሲናገርህ በሰማኸው ቃል በንስሃ ትመለሳለህ ወይስ በእልከኛነት መንፈስ በመልዕክቱ አምጪ ላይ ትነሳለህ?
5. ቁ20-26 ላይ ኢየሱስን ከአፉ በሚወጣ ቃል ለማጥመድ የተላኩት ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩ ነው ከዚህ ክፍል የምንረዳው? እነዚህ ተላኩ የተባሉት ሰዎች ፈተናቸውን ለኢየሱስ ከማቅረባቸው በፊት የኢየሱስን ማንነትና ተግባሩን አስመልክተው የሚናገሯቸውን ነገሮች በዝርዝር ተናገር። ቁ20 ላይ ሰዎቹ የተላኩት "ከአፉ በሚወጣ ቃል ለማጥመድ" ነው የሚለው፤ ከዚህ አንጻር በአሁኑ ጊዜ ላሉት የወንጌል አገልጋዮች ይህ ሃሳብ በማስጠንቀቂያነት ሊያገለግል የሚችለው እንዴት ነው?
6. ቁ2፣ ቁ22፣ ቁ28ትንና የመሳሰሉትን ስንመለከት ኢየሱስ ከተለያዩ ዓይነት ሰዎች የተለያዩ ዓይነት ጥያቄዎች ሲቀርቡለትና ምላሽ ሲሰጥ እንመለከታለን፤ ይህ በኢየሱስ ህይወት የምንመለከተው ነገር በ1ኛ ጼጥ 3፡15 ላይ ለአማኞች የተሰጠውን መመሪያ የሚያሟላው በምን መንገድ ነው? ቁ39 ላይ "አንዳንድ ጻህፍትም፤ መምህር ሆይ መልካም ተናገርክ አሉት።" ይላል። ጻህፍት ኢየሱስን ሊገድሉ የሚፈልጉ ሆነው እያሉ ለምን ይመስልሃል ስለ ትንሳኤ የሰጠው መልስ ደስ ያሰኛቸው?
7. በቁ39 ላይ ኢየሱስ ስለእርሱ መልካም የተናገሩለትን ሰዎች በቁ45-47 ላይ ስንመለከት ስለእነርሱ የሚናገረው ነገር ምን እንደነበረ በዝርዝር ተናገር። ስለጻህፍት የተናገረውን ነገር የሰሙት እነማን ናቸው? ጻህፍት ለኢየሱስ "መልካም ተናገርክ" በማለታቸው ጥፋታቸውን ከመናገር ወደኋላ እንዳላለ እንመለከታለን፣ እኛስ ለሚያሞካሹን ሰዎች ስህተታቸውን በእግዚአብሄር ቃል ለመገሰጽ ድፍረት አለን ወይ?
8. ቁ27-33 ላይ መለስ ብለን ስንመለከት የእግዚአብሄርን ቃል ሰዱቃውያኑ የተጠቀሙበት ለምን ዓይነት ነገር ነበረ? አንተስ ራስህን እንድታይበት የተሰጠህን የህይወት ቃል ሰዎችን በክርክር ለመርቻ፣ ወይም ራስህን ለማጽደቂያ፣ ወይንም ደግሞ ሌሎችን ለመኮነኛ ትጠቀምበታለህ ወይ? እግዚአብሄር ቃሉን ሲሰጠን እንድንታዘዘውና ህይወት እንዲሆንልን እንጂ ከሰዎች ጋራ በሚኖረን ጦርነት መሳሪያ አድርገን እንድንጠቀምበት አይደለም።

# ጥናት ሃያ ስድስት ሉቃስ 21፡1-38

የጥናት ዓላማ፡- ጌታችን እንደተናገረው፤ ገደብ የለሽ ህይወትና ስለኑሮ መጨነቅ ጌታን በተጠንቀቅ ከመጠበቅ ሊያዘናጉን የሚችሉ ነገሮች እንደሆኑና፤ ነገር ግን በእነዚህ ፈንታ በነገሮች ሳንዘናጋ ሁልጊዜ ተግቶ መጸለይን ልማዳችን ማድረግ እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እንግዲህ በገደብ የለሽ ህይወት፣ በመጠጥ ብዛትና፣ ስለኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ ድንገት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ…ሁልጊዜ ተግታችሁ ፀልዩ።" ሉቃ 21፡34-36

1. ሉቃስ 21፡1-38 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-4 ላይ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ስንት ዓይነት ሰዎች እንዳሉና፣ እነዚህም ሰዎች እያንዳንዳቸው ያደርጉ የነበሩትን ነገር በመዘርዘር ተናገር። በቤተ መቅደሱ ውስጥ እየተካሄደ የነበረውን የመባ አሰጣጥ ሁኔታ ያስተዋለው ኢየሱስ፤ ስጦታቸውን ያወዳደረበትን መንገድ ስንመለከት፤ በኢየሱስ እይታ የሴትየዋ ስጦታ በልጦ የተገኘበት ዋና ምክንያት ምን ነበረ?
2. በቁ1-4 ላይ ኢየሱስ ሲያደርጉ በተመለከተው ነገር ላይ በመመርኮዝ ሁኔታውን ለማስተማር እንደተጠቀመበት ተመልክተናል፤ በዚህ ከቁ5 ጀምሮ እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ማለት ይቻላል፤ ላስተማረው ትምህርት መነሻ ሆኖ የምታየው ነገር ምንድነው? ከቁ5-7 ላይ ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ ቤተ መቅደሱ እንደሚፈርስ የሰነዘረው ሃሳብ በደቀ መዛሙርቱ አዕምሮ ውስጥ የፈጠሩዋቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን የሚሉ ናቸው?
3. በቁ8 እና 9 ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ቢያንስ ሶስት ማስጠንቀቂያዎችን ሲሰጣቸው እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስት ማስተንቀቂያዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ በኢየሱስ ስም እንደሚመጡ የተነገረላቸው ሰዎች ሰዎችን ለማሳት የሚናገሯቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ከኢየሱስ አነጋገር ስንረዳ ስለጦርነትና ስለ ሕዝብ ዓመጽ በምንሰማበት ጊዜ ለምንድነው መደንገጥ የማይኖርብን?
4. ቁ12 ላይ "ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት…" ሲል የትኛውን ነገር ሲያመለክተን ነው? በቁ10 እና 11 ላይ መጨረሻው ከመምጣቱ በፊት መሆን አለባቸው በማለት የተናገራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝር። በቁ12 ላይ የምናነባቸውና በክርስቶስ ተከታዮች ላይ ይደርሳሉ ተብለው የተነገሩት ነገሮች፤ ገና ከፊታችን የሚጠብቁን ነገሮች ናቸው ወይስ ሰዎች እስከዛሬ በዚህ ውስጥ አልፈው አብቅቷል የሚል ሃሳብ እንዳላችሁ ተወያዩበት።
5. በቁ13-19 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ትኩረት ሰጥተን ስንመለከት፤ አማኞች በሌላ በምንም መንገድ ማግኘት የማይችሉት ነገር ግን፤ በመያዛቸው፣ በመሰደዳቸው፣ ወደ ወህኒ በመግባታቸውና፣ በነገሥታትና በገዢዎች ፊት በመቅረባቸው ብቻ ማግኘት የሚችሉት አንድ ትልቅ ነገር ምንድነው ይለናል ጌታችን? ቁ14-15 ላይ ለምንድነው ጌታ በነገሥታትና በገዢዎች ፊት ስንቀርብ እንዳንፈራና፤ ምን መናገር እንደሚኖርብን መጨነቅ እንደማይኖርብን የተናገረው?
6. በቁ16 ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች በደህናው ጊዜ ምን የሚያደርጉልን ዓይነት ሰዎች ናቸው? ከቁ13-19 በምናነበው ክፍል ውስጥ አማኞች ስለ ክርስቶስ ሲሉ ሊከፍሉት ስላላቸው ዋጋ እናያለን፤ ለጌታ ተብሎ እንደሚከፈል ከተነገሩን ነገሮች መሃል ስታስበው የሚከብድህ ወይም የሚያስፈራህ የትኛው ነው? በዚህ ሁሉ ውስጥ ለሚያልፉት ልጆቹ ጌታ የገባላቸውን አንድ የተስፋ ቃል በዚሁ ክፍል ውስጥ እንመለከታለን፤ ይህ የተስፋ ቃል ምንድነው?
7. ቁ20-28 በአንድነት ይነበብ። በተለይ ከ22-23 ያለውን ክፍል ስንመለከት ጌታ ይህ ሁሉ የሚሆንበትን ምክንያት ግልጽ አድርጎ ይናገራል፤ የዚህ ሁሉ መከራ ምክንያት ምንድነው ነው የሚለን? ቁ25-28 ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ሁሉ ሲፈጸሙ በአለም ያሉት ሰዎች ስሜታቸው ምን ይመስላል? እነዚሁ ሁኔታዎች ሁሉ መፈጸም ሲጀምሩ የሚመለከተው አማኝስ ምን ዓይነት እርምጃዎችን እንዲወስድ ነው የተነገረው?
8. በቁ34-37 ላይ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ሲሰጥ የምናያቸው ማስጠንቀቂያና ምክር ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር። ጌታ የሰጠውን ማስጠንቀቂያና ምክር ልብ ብለህ ትከታተላለህ ወይ? በተለይ ገደብ የለሽ ህይወትና ስለኑሯችን አብዝተን መጨነቅ፤ ጌታን በተጠንቀቅ ከመጠበቅ የሚያዘናጉን ነገሮች እንደሆኑና፤ በነዚህ ፈንታ ግን ሁልጊዜ ተግቶ መጸለይን መለማመድ ይኖርብናል።

# ጥናት ሃያ ሰባት ሉቃስ 22፡1-71

የጥናት ዓላማ፡- በህይወታችን የሚያሳዝንና የሚያስጨንቅ ነገር ሲያገኝን፤ እንደ ደቀ መዛሙርቱ በእንቅልፍ ወይም በሌላ ዓይነት ነገር ለማሸነፍ መሞከር እንደማይኖርብንና፤ እንደ ኢየሱስ ተግተን በመጸለይ ድል ማድረግ እንደምንችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እጅግ ተጨንቆ በብርቱ ይጸልይ ነበረ…ከጸሎትም ተነስቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣ፤ እነርሱም ከሃዘን የተነሳ ተኝተው አገኛቸውና፤ ለምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነስታችሁ ጸልዩ አላቸው።" ሉቃ 22፡44-45

1. ሉቃስ 22፡1-71 በአንድነት ይነበብ። ቁ1-6 ላይ የሰፈረውን ታሪክ ስናነብ የካህናት አለቆችና ጻህፍት በአንድነት የሚመክሩትና ለማድረግ የሚሹት ነገር ምን ነበረ? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ የአስቆሮቱ ይሁዳ ሰይጣን እንደገባበት ወዲያው ምን ሲያደርግ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? በዚህ ሥፍራ የኢየሱስን ሞት ለሚፈልጉት የሁኔታው መገጣጠም ምን ዓይነት ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ይመስልሃል? የሁኔታዎችን መገጣጠም የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንደሆነ አስበህ ታውቃለህ ወይ?
2. በቁ10-13 ውስጥ ኢየሱስ በጣም ዝርዝር የተሞላው መመሪያ ለሚልካቸው ደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ ይታያል። እነዚህን መመሪያዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው? ደቀ መዛሙርቱስ በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ሲሄዱ ሁኔታውን እንዴት ሆኖ ነው ያገኙት?
3. ከቁ24-30 ባለው ክፍል ውስጥ በደቀ መዛሙርቱ መሃል ትልቅ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ የተገኘው ነገር ምን ነበረ? በተለይም ቁ26 ላይ ኢየሱስ "በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይሁን" እያለ ሲናገር፤ የእርሱን ተከታዮች ከማን ጋራ እያወዳደረ ነው ሲናገር የምናየው? ቁ27ትን ስናነብ፤ ኢየሱስ የራሱን ህይወት በማንሳት ለደቀ መዛሙርቱ ትምህርት እንዲቀስሙ ሲናገር እናየዋለን፤ በዚህ ቁጥር ላይ ምን ሊናገራቸው የፈለገው ዋነኛው ሃሳብ ምንድነው?
4. ቁ31 እና 32ትን ስንመለከት ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ የማያውቁት ኢየሱስ የሚነግራቸው አንድ እውነት ምን ትመለከታለህ? በነዚሁ ቁጥሮች ላይ አተኩረን ስንመለከት፤ ሰይጣን አንድ ፍላጎት እንደነበረውና ያንን ፍላጎቱን ለማሟላት ማድረግ የነበረበት አንድ ነገር ምን ነበረ? ጠላታችን ምን ጊዜም እኛን ለማጥፋትና ለማዋረድ እንደማይተኛ፤ ሆኖም ያለ አምላካችን ፈቃድ አንዳች ሊያደርገን እንደማይችል ልንረዳ ያስፈልገናል።
5. ቁ35-38 ላይ ደቀ መዛሙርቱ ጌታ አስቀድሞ ያለ ኮረጆና ያለ ከረጢት በላካቸው ጊዜ ምንም እንዳልጎደለባቸው ይነግሩታል። ቁ36-38 ከዚህ በኋላ ማድረግ ስለሚኖርባቸው ነገር ከነገራቸው በኋላ፤ በተለይም በቁ38 ላይ ሁለት ሰይፍ እንዳላቸው ሲነግሩት፤ "ይበቃል" ያለው አነጋገር ሁለት ሰይፍ ካለን እናሸንፋቸዋለን ለማለት ነው ወይስ ምን ማለቱ ይመስልሃል? ቁ33ት ላይ በጴጥሮስ ቃል ኪዳንና፤ በቁ56-62 በምናነበው እውነት መሃል ያለው መለያየት ምን እንደሆነ ተናገር። አንተስ እንደ ጴጥሮስ እሁድ በሞቅታ ቃል ገብተህ ሰኞ ያፈረስክበት ቀን ይኖር ይሆን?
6. ቁ39 ላይ "ኢየሱስ እንደ ልማዱ ወጥቶ ወደ ደብረዘይት ተራራ ሄደ" በማለት ይነግረናል። ኢየሱስ እየተፈለገ እንደሆነ፣ ከተከታዮቹም አንዱ ይሁዳ ደግሞ በደንብ አጥርቶ ያለበትን ቦታ ሊመራቸው እንደሚችል እያወቀ ለምንድነው ኢየሱስ ይሁዳ እንዳያገኘው ቦታ የመቀየር ታክቲክ ያልተጠቀመው? ኢየሱስን ለመያዝ በመጡ ጊዜ ጴጥሮስ የሰው ጆሮ ቆርጦ በቁ51 ላይ ኢየሱስ እዚያው የሰውየውን ጆሮ እንደፈወሰ እናያለን፤ በተሰራው ተአምር ሰዎቹ አይተው ወደ እምነት አለመምጣታቸው ምን ያስተምረናል?
7. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሥጋ መሳሪያ ማለትም የነበረውን ሰይፉን ተጠቅሞ የሰውን ጆሮ ያቆሰለው ጴጥሮስ፤ በሐዋ ሥራ 2 ላይ ስንመለከተው የሶስት ሺህ ሰዎችን ልብ በመፈወስ ወደ ህይወት ያመጣው ምን በመጠቀም ነበረ? በቁ63-65 ላይ በጠባቂቆቹ በማሾፍም ቢሆን እንዲያረጋግጥ እንደተጠየቀ፤ በቁ66-71 ደግሞ ለካህናት አለቆቹ ስለማንነቱ ተጠይቋል። እነዚህ ሁለት ስለማንነቱ የተጠየቃቸው ጥያቄዎች ምንና ምን ነበሩ?
8. መለስ ብለን ቁ44 እና 45ትን ስንመለከት ኢየሱስም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ በሃዘንና በጭንቀት ውስጥ እንደነበሩ እናያለን። ያሉበትን ሁኔታ ለማሸነፍ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ የወሰዱት መፍትሄ የሚለያየው እንዴት ነው? አንተስ ስትጨነቅና ስታዝን መፍትሄህ የደቀ መዛሙርቱ አይነት ነው ወይስ የኢየሱስ? ሃዘንና ጭንቀት በህይወታችን ሲያገኘን መፍትሄ ሊሆንልን የሚችለው እንደ ጌታችን በጸሎት ወደ አምላካችን መቅረብ ብቻ ነው።

<u>ጥናት ሃያ ስምንት ሉቃስ 23፡1-56</u>

የጥናት ዓላማ፡- አካባቢያችን ሁሉ በኢየሱስ ላይ በሚነሳበት ወቅት፤ እኛም ከሌሎች ጋራ ከማበር እነርሱ የሚሉትን በማለት ወይም ደግሞ በዝምታ ከማለፍ ይልቅ፤ ዮሴፍ እንዳደረገው በሃሳባቸው እንደማንስማማና እንደምንቃወም በግልጽ ማሳወቅ እንደሚኖርብን ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነ አንድ ዮሴፍ የሚባል በጎና ጻድቅ ሰው ነበረ፤ ይህ ሰው በሸንጎው ምክርና ድርጊት አልተባበረም ነበረ።” ሉቃ 23፡50-51

1. ሉቃ 23፡1-56 በአንድነት ይነበብ። ከቁ1-4 ላይ ስንመለከት እነዚህ ብዛት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን በጲላጦስ ፊት የሚከሱባቸው ሶስት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? ከእነዚህ ከሶስት ክሶች ውስጥ ምን ያህሉ እውነት፣ ምን ያህሉ ደግሞ የውሸት ክስ ናቸው? ኢየሱስ ከተከሰሰባቸው ሶስት ዓይነት ክሶች መሃል ጲላጦስ ትኩረት ሰጥቶ ለማወቅ የፈለገውና ያተኮረው በየትኛው ክስ ላይ ነው?
2. ቁ5-11 ላይ ስናነብ ሄሮድስ ኢየሱስን ለመገናኘት ለብዙ ጊዜ ይፈልግ እንደነበረ እናያለን፤ ሄሮድስ ኢየሱስን ለማየት የሚፈልግበት ዋነኛ ምክንያት ለምን ነበረ? ሄሮድስ ኢየሱስን ባገኘበት ወቅት ከእርሱ ለማግኘት የሚፈልጋቸውን ነገሮች ማግኘት ችሏል ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ። በቁ11 ላይ ሄሮድስ ከኢየሱስ የሚፈልገውን ማግኘት ሳይችል ሲቀር ያረገው ነገር ምን ነበረ? ኢየሱስን ወደ እኛ እንዲመጣ የምንፈልገው እንደ ሄሮድስ ከእርሱ የሚገኙትን ነገሮች ፈልገን ነው ወይስ ኢየሱስን ራሱን ፈልገን?
3. ጲላጦስን በቁ12-19 ላይ ስንመለከተው፤ የኢየሱስን ንጽህና በማረጋገጥ ለከሳሾቹ መልስ ይሰጣል። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጲላጦስ የኢየሱስን ንጹህ መሆን የሚናገርባቸው ሶስት ቦታዎች የትኞቹ እንደሆኑ ተናገር። ህዝቡ የኢየሱስ ንጽህና እየተነገራቸው በቁ18-19 ውስጥ ደግሞ የበርባንን ማንነትም እያወቁ፤ ምርጫው ሲሰጣቸው ማን እንዲፈታላቸው ነው ሲጠይቁ የሚታየው? ከዚህ ሁኔታ መማር የምንችለው እውነት ምን ይመስልሃል?
4. ቁ20-25 ላይ ስናይ ለእነዚህ የኢየሱስ ከሳሾች ሃሳባቸውን ይቀይሩ እንደሆነ በማሰብ ጲላጦስ ምን ያህል እድል ነበረ የሰጣቸው፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስናነብ እነዚህ በከሳሽነት የቀረቡት ሰዎች በኢየሱስ ላይ የነበራቸው ጥላቻ ምን ያህል ስር የሰደደ መሆኑን የሚያሳዩትን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር።
5. ከቁ26 እስከ 31 በሚገኙት ቁጥሮች ላይ እነማንን ትመለከታለህ? ኢየሱስ በቁ28 ላይ “እናንት የኢየሩሳሌም ሴቶች፤ ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ፤ ለእኔ አታልቅሱ” ብሎ ሲናገር፣ ለምን ይመስልሃል ለእርሱ እንዲለቀስለት ያልፈለገው? ሴቶቹ ለራሳቸውና ለልጆቻቸው እንዲያለቅሱስ የተናገረበት ምክንያት ለምንድነው?
6. በቁ32-43 ላይ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች የኢየሱስን ሞት አስመልክቶ የተለያዩ አይነት ነገሮችን ሲያደርጉ እንመለከታለን። በነዚህ ቁጥሮች አድራጊዞቹን ሰዎችና ሲያደርጓቸው የምታያቸውን ነገሮች አንድ በአንድ ዘርዝር። ኢየሱስ በተሰቀለበት በዚያን ወቅት አንተ በዚያ ኖረህ ብትሆን ራስህን ከየትኞቹ ሰዎች ጋራ የምታገኝ ይመስልሃል?
7. በቁ32-43 የኢየሱስን እስራትና ሞት አስመልክቶ በአብዛኛው ሰዎች ያደረጓቸውን ነገሮች ላይ በማተኮር የተለያዩ ነገሮች መመልከት ሞክረናል፤ በቁ44-46 ላይ ደግሞ በእግዚአብሄር የተከናወኑ ነገሮችን እናያለን፤ እነዚህ አምላክ ያከናወናቸው ድርጊቶች ምን ምን ነበሩ? በቁ47 ላይ የምንመለከተው የመቶ አለቃ በዚያን ሰዓት የሆነው ነገር የኢየሱስን ጻድቅነት እንዳረጋገጠለትና እንዳመሰገነ ይታያል፤ የጻድ ቁ መሞት ነው ወይስ ምን ነበረ ሰውየውን ለምስጋና ያበቃው?
8. በቁ50-56ት ላይ የምናየው ዮሴፍ በአይሁድ ሸንጎ አባልነት ያገለግል እንደነበረ እናነባለን፤ ዮሴፍ የተሰማራበት የሥራ መስክ በተለይም ኢየሱስን አስመልክቶ በሆነው ነገር ላይ አስቸጋሪ ሊሆን የሚችለው ለምንድነው? አንተስ በኢየሱስ ላይ በሚነሱ ሰዎች በተከበበከበት ሰዓት ከእርሱ ጋራ ለመቆም ትደፍራለህ ወይ? አካባቢያችን ሁሉ በኢየሱስ ላይ በሚነሳበት ሰዓት፤ እኛም ከሌሎች ጋራ ከማበር ወይም በዝምታ ከማለፍ ይልቅ የቆምንበትን ማሳወቅ ይኖርብናል።

# ጥናት ሃያ ዘጠኝ ሉቃስ 24፡1-53

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ የራሱን ድርሻ በመወጣት መንፈሱን በውስጣችን እንዲኖር የሰጠን ስለሆነ፤ እኛ ደግሞ ለእርሱ ምስክሮች በመሆን ለሰዎች ሁሉ የንስሃን መልዕክት ማድረስ እንደሚኖርብን ለማሳሰብ።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ። እኔም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ሃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።” ሉቃ 24፡48-49

1. ሉቃ 23፡1-56 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-8 ላይ ስንመለከት፤ ወደ የኢየሱስን ሬሳ ሽቱ ለመቀባት ይዘው የሄዱት ሴቶች መቃብሩ አጠገብ በደረሱ ጊዜ ግራ እንደተጋቡ እናያለን፤ ሴቶቹን ግራ ያጋባቸው ነገር ምን ነበረ? ቁ5-8 ላይ መላዕክቱ በመቃብሩ አጠገብ ላገኟቸው ሴቶቹ ካስተላለፉት መልዕክት ከምንረዳው፤ ሴቶቹ በገጠማቸው ሁኔታ ግራ መጋባታቸው ምንም የሚያስገርም ነገር እንዳልሆነ ማየት የሚቻለው ለምንድነው?።
2. ቁ1-12 ውስጥ በተመለከትነው ታሪክ ውስጥ ሁለቱ መላዕክት የገለጠላቸው ሴቶች ቁጥር ቢያንስ ቢያንስ ስንት ሊሆኑ እንደሚችል ተናገር። በቁ11 ላይ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሲናገር “እነርሱ ግን ሴቶቹ የተናገሩትን ቃል መቀባዥር ስለመሰላቸው አላመኗቸውም።” ይላል። በዚህ ሥፍራ መልዓኩን ያየችው አንዷት ሴት ብቻ እንዳልሆነች እናውቃለን፤ የሴቶቹ ቁጥር ከአንድ በላይ መሆኑ የደቀ መዛሙርቱን አለማመን የሚያጎላው ለምንድነው? በደቀ መዛሙርቱ አለማመን ያልተባበረ ሰው ታያለህ ወይ? አንተስ ከብዙሃን አለማመን ራስህን መለየት ትችላለው ወይስ ባለማመን ከሰፊው ህዝብ ጋራ ትተባበራለህ?
3. እነዚህ ሁለት ሰዎች በኤማዖስ መንገድ ላይ እየተጓዙ ሳሉ ይነጋገሩበት የነበረው ርዕስና በምን ላይ የተመሰረተ ነበረ ከቁ17-20 ላይ በመመርኮዝ ተናገር። ቁ21-24ትን ስንመለከት ቀለዮጳና ጓደኛው ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ የነበራቸው አመለካከትና፤ አሁን በዚህ ጊዜ ደግሞ ስላላቸው አመለካከት ምን መረዳት የምንችለው ነገር አለ?
4. ኢየሱስ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ የተረከሉትን ሁሉ ከሰማ በኋላ በቁ25-27 ውስጥ ሰዎቹ በመንፈሳዊ ህይወታቸው የሚገኙበትን ሁኔታ ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ሁለት አባባሎች ምንና ምንድናቸው? በቁ25 ኢየሱስ “ልባችሁ ነብያት የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ” ብሎ ሲናገር፤ በተለይ በምን ላይ ያተኮረውን ትንቢት ይመስልሃል? ኢየሱስ አለማመናቸውን ከነቀፈ በኋላ በቁ27 ላይ ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? ኢየሱስ አለማመናችንን ቢነቅፍም እንኳን፤ በትዕግሥት ማስተማሩንም ደግሞ አያቋርጥም።
5. በቁ27-32 ያሉትን ቁጥሮች ስንመለከት ኢየሱስ ከእነዚህ ሰዎች ጋራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዳካሄደ ቁ27 ላይ መመልከት እንችላለን፤ እነዚህ ሰዎች ግን ዓይኖቻቸው የተከፈተውና ኢየሱስን ማየት የቻሉት መቼ ነበረ? በቁ32 ላይ ከራሳቸው አንደበት ከምንሰማው ምስክርነት ደግሞ ቃሉን ሲሰሙ በውስጣቸው ይሰማቸው ስለነበረው ስሜት እን እንረዳለን? ከነዚህ ሁለት ሃሳቦች የእግዚአብሄር ቃልና ከክርስቶስ ጋራ ሊኖረን ስለሚገባው ህብረት ምን እንማራለን? የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ብቻ ሆነን አንቅር።
6. በቁ33-35 ላይ ስንመለከት በኢየሩሳሌም የቆዩት ደቀ መዛሙርትና ከኤማዖስ የተመለሱት ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ዋነኛ የመወያያ ርዕሳቸው ምን ነበረ? በኢየሱስ መነሳት ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ያንን ያህል እርግጠኛ ከሆኑና በተጨባጭ አረጋገጡ ከተባለ፤ ለምንድነው ታዲያ በቁ37 ላይ ኢየሱስ ተገልጦ ሰላም ለእናንተ ይሁን ሲል ፍርሃትና ድንጋጤ ሞልቶባቸው መንፈስ ያዩ የመሰላቸው?
7. ቁ44-49 ላይ ስናነብ ኢየሱስ በሙሴ ሕግ፣ በነብያትና፣ በመዝሙር መጻህፍት ስለ እርሱ የተጻፈው ሁሉ እንደሚፈጸም ይነግራቸዋል። ከተጻፉት ከነዚህ ነገሮች መሃል በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተፈጽሞ የምንመለከተው ነገር ምንድነው? በቁ45 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲያደርግ የምናየው ነገር ምንድነው? ከዚህ በፊት ለዓመታት ቃሉን ሲያስተምራቸው እንደኖረ እናውቃለን፤ ታዲያ በዚህ ቁጥር ላይ ለደቀ መዛሙርቱ ያደረገውን ነገር ስትመለከት ምን የምትማረው ነገር አለ?
8. ቁ48 እና 49ኝን ስንመለከት ኢየሱስ ከእነርሱ ከተለየ በኋላ የደቀ መዛሙርቱና የኢየሱስ ድርሻ ምን መሆን እንደሚኖርበት ኢየሱስ ተናግሯል፤ የኢየሱስና የደቀ መዛሙርቱ ድርሻ ምንድነው? አንተስ በተሰጠህ የመንፈስ ቅዱስ ሃይል ሃላፊነትህን እየተወጣህ ነው ወይ? ኢየሱስ የራሱን ድርሻ በመወጣት መንፈሱን የላከልን ስለሆነ፤ እኛ ደግሞ ለእርሱ ምስክሮች ለመሆን ቁ47 እንደሚናገረው፤ ካለንበት ሥፍራ ጀምረን ለህዝቦች ሁሉ ወንጌልን የማድረሱን በእኛ ሃላፊነት ሥር አኑሮታል።